

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት 2006

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 2

መግቢያ ........ 2

የማዕከሉ ራዕይና ተልዕኮ ........ 3

የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር ........ 3

የማዕከሉ አላማ ........ 4

የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር ........ 4

የማዕከሉ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ........ 5

የማዕከሉ የፋይናንስ ምንጭ ........ 5

ማዕከሉ የተቀበላቸው እና ያስመረቃቸው ተማሪዎች ብዛት ........ 6

የኦዲቱ አላማ ........ 6

የኦዲት አካባቢ (POTENTIAL AUDIT AREA) ........ 6

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES) ........ 6

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት ........ 7

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 7

መደበኛ/የቀን/ ስልጠና የሥራ ሂደት መግለጫ (SYSTEM DESCRIPTION) ........ 7

ተከታታይ/ የማታ/ ስልጠና የሥራ ሂደት መግለጫ ........ 8

ክፍል ሁለት ........ 9

የኦዲት ግኝቶች ........ 9

የስትራቴጂክ ዕቅድ እና ዓመታዊ ዕቅዶች የሚዘጋጁ እና በዕቅዱ መሰረት መስራቱን በተመለከተ፣ ........ 9

በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ብቁና የሰለጠነ የሰው ኃይል ከማፍራትና ስልጠናው በተጠናከረ ሁኔታ እንዲሰጥ የሚያስፈልጉ ሞጅሎች ስለመኖራቸው ........ 10

ለተማሪዎች ስልጠና የሚሰጥበት እና የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት መሳሪያዎች የተሟሉ መሆናቸውን በተመለከተ ........ 12

ችግር ፈቺ የሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎች የተከናወኑ መሆኑን በተመለከተ ........ 14

ለተማሪዎች በስልጠና ወቅት የክፍል ጊዜ ብክነት እንዳይኖርና የስልጠና አሰጣጥ ሂደትን መቆጣጠሪያ ስርዓት የተዘረጋ ስለመሆኑ፣ ........ 15

በማዕከሉ ለተማሪዎች የሚሰጥ የኪስ ገንዘብ በወቅቱ የሚደርሳቸው ስለመሆኑ ........ 17

ለማዕከሉ አስተማሪዎች የስራ መዘርዝር የሚደርስ መሆኑን በተመለከተ ........ 19

በማዕከሉ ተማሪዎች የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት ሞዴል ሆቴል መኖሩን በተመለከተ ........ 20

በገነት ሆቴል የሚገኙ የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማስተማሪያ ክፍሎች ለመለወጥ የሚደረግ የዕድሳት ስራን በተመለከተ፣ ........ 21

በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት እና ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት የተዘረጋ ስለመሆኑ፣ ........ 28

የማዕከሉ የመረጃ አያያዝ የተጠናከረ መሆኑን በተመለከተ ........ 29

ክፍል ሶስት ........ 31

መደምደሚያ ........ 31

ክፍል አራት ........ 34

የማሻሻያ ሃሳቦች ........ 34

አባሪ 1 ........................................................................................................................................................ 37
የመመዘኛመስፈርቶች ........................................................................................................................................ 37

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ቱሪዝም በዓለም ላይ ፈጣን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ከሚያስመዘግቡ ዘርፎች መካከል ዋነኛውና ቀዳሚው ነው፡፡ የቱሪዝም መስፋፋት ቀጥተኛ የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘቱም በተጨማሪ ባለው ልዩ ባህሪ የተነሳ የተለያዩ የኢኮኖሚ ክፍሎችን በማነቃቃት የገቢ ስርጭትን በማመጣጠን ለድህነት ቅነሳና ለልማት አስተዋፅዎ የሚያደርግ ሲሆን የሥራ ዕድልም ፈጣሪ ነው፡፡
2. ኢትዮጵያ ይህንን ላቅ ያለ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኘው የቱሪዝም ዘርፍ ለማሳደግ መሠረት የሆኑት የቅድመ ታሪክ፣ የባህልና የተፈጥሮ መስህቦች ባለቤት ከመሆኑዋም በተጨማሪ ትጉህና እንግዳ የመቀበል ባህል ያላቸው የብሄር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አገር ናት፡፡
3. አገራችን ያሏትን የላቀ የቱሪዝም አቅም ለልማት እና ለለውጥ ለማዋል እንዲቻል መንግስት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ውስጥ የገቢ እና የሥራ ፈጣሪነትን እንደ አንድ የልማት መሣሪያ አድርጎ አስቀምጧል፡፡ ይህን ለድህነት ማስወገድ እና ለልማት ቀጥተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርግ ኢንዱስትሪ በጥቅም ላይ ለማዋልና ተጨባጭ የሆነ ለውጥ በማምጣት በዓለም ዓቀፍ የቱሪዝም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል፡፡ ለዓለም አቀፍ የቱሪዝም ዘርፍ ተወዳዳሪነት ከሚያበቁ በርከት ያሉ ምክንያቶች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ደግሞ ለቱሪስቶች በሥነምግባር፣ በዕውቀት፣ በክህሎት እና በአደረጃጀት የተቃኘ አገልግሎት መስጠት ነው፡፡
4. ሆቴሎችም አገራችን ለቱሪዝም ጉብኝት የሚመጡትን እንግዶች በመቀበል አገልግሎት በመስጠትም ሆነ በሌሎች አገልግሎቶች የምታገኘው ገቢ የላቀ ነው፡፡ በመሆኑም በሆቴልም ሆነ በቱሪዝም ሥነምግባር፣ ዕውቀት፣ ክህሎት እና አደረጃጀት ተወዳዳሪነት ያለው አገልግሎት ማቅረብ የሚቻለው ከምንም በላይ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሰለጠነ የሰው ኃይል በተሟላና በበቂ ሁኔታ ለዘርፉ ማቅረብና መጠቀም ሲቻል ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል በሀገራችን የሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪ እንዲፈነጥቅ ፋና ወጊ የሆነ የመጀመሪያው የመንግስት ተቋም ነው፡፡ ይህ ተቋም ከተመሰረተበት ከ1961 ዓ.ም ጀምሮ ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በማሰልጠንና በማቅረብ ዛሬ በሀገራችን በመሪነት ከሚገኙት የአገልግሎት ዘርፎች አንዱ የሆነውን የሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪ የላቀ አስተዋጽኦ ያበረከተና እያበረከተ የሚገኝ አንጋፋ ተቋም ነው፡፡

5. ይህ አንጋፋና ፋናወጊ የማሰልጠኛ ማዕከል መንግስት በሰጠው ልዩ ትኩረት በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 174/2002 በአዲስ መልክ ተቋቁሞ ተገቢውን የትምህርትና ሥልጠና የማማከር እንዲሁም ጥናትና ምርምር ሥራ እያካሄደ ይገኛል፡፡

## <u>የማዕከሉ ራዕይና ተልዕኮ</u>

**ራዕይ**

6. በላቀ ሥልጠና፣ በጥናትና ምርምር እና በምክር አገልግሎት በ2012 ዓ.ም በምስራቅ አፍሪካ አንደኛ የሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች ማፍለቂያ ማድረግ፡፡

**ተልዕኮ**

7. በሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪ ተፈላጊ የሆነ ብቃትና ጥራት ያለውን የሰው ኃይል ለማፍራት ተገቢውን ስልጠና መስጠት፣ ለኢንዱስትሪው እድገት ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ የምክር አገልግሎት በመስጠት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን በማሻሻል ተመራጭ የቱሪስት መዳረሻ በመሆን ሃገሪቱ በቱሪዝም ሃብቷ ከፍተኛ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል፡፡

## <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

8. በማዕከሉ መዋቅር መሠረት ማዕከሉ በቦርድ የሚተዳደርና ዋና ዳይሬክተር እና ም/ዋና ዳይሬክተር ያሉት ሲሆን ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-
   1. የማዕከሉን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣
   2. የማዕከሉን መዋቅርና የሥራ መመሪያዎችን ያፀድቃል፣
   3. የማዕከሉን ዓመታዊ የሥልጠናና የሥራ ኘሮግራም፣ የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድ እንዲሁም በጀት መርምሮ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ በሚኒስቴሩ አማካይነት ለመንግስት ቀርቦ የፀደቀው ዕቅድ፣ በጀትና ኘሮግራም በማዕከሉ በግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፤
   4. የማዕከሉን ሥራ አፈፃፀም ሪፖርት እየገመገመ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
   5. የማዕከሉን ሥልጠናና የአካዳሚክ መመሪያዎችን ያፀድቃል፤ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
   6. ማዕከሉ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ካሉ መሰል ተቋሞች ጋር የሚያደርጋቸውን ስምምነቶች መርምሮ ያፀድቃል፡፡

## የማዕከሉ አላማ

9. ማዕከሉ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

   1. የቱሪዝም ኢንዱስትሪን ዕድገትና ልማት ለማፋጠን የሚያስፈልገውን በጽንሰ ሐሳብና በተግባር የሰለጠነ የሰው ኃይል በጥራትና በብቃት ለማፍራት የቅድመ ሥራ ስምሪት ሥልጠና መስጠት፤
   2. በቱሪዝም ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የአጭርና የረዥም ጊዜ የሙያ ማሻሻያና የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት፤
   3. በሆቴልና በቱሪዝም ሙያ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ በዘርፉ የልዕቀት ማዕከል በመሆን ለመሰል ተቋማት የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፤
   4. ለቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች አስፈላጊውን የምክር አገልግሎት መስጠት

የሚሉት ናቸው፡፡

## የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር

10. ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

    1. የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶችን በማውጣት ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የቅድመ ሥራ ስምሪት እና የሥራ ላይ ሥልጠና ይሰጣል፤
    2. ለሆቴልና ቱሪዝም መስክ እድገትና ልማት ጠቃሚ የሆነ ጥናትና ምርምር ያካሂደል፣ ግኝቶችንም ያሰራጫል፤
    3. ለቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
    4. በሆቴልና ቱሪዝም መስክ በዓበይትና ወቅታዊ ጉዳዮች፣ በምርምር ውጤቶችና አዳዲስ አስተሳሰቦች ላይ ሴሚናሮችን፣ ሲምፖዚየሞችንና ወርክሾፖችን ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፣
    5. በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት ሞዴል ሆቴሉን ይቆጣጠራል፣ የአገልግሎት ጥራቱንም ያሳድጋል፣
    6. በዘመናዊ ቴክኖሎጂና በሌሎች ዘዴዎች እየተገለገለ አቅሙን በመገንባት የስልጠና ብቃቱን ያሻሽላል፤
    7. በሃገር ውስጥና በሌሎች ሃገሮች ከሚገኙ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነት ይመሰርታል፤
    8. ለሚሰጣቸው የሥልጠና እና የምክር አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ዋጋ ያስከፍላል፤
    9. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
    10. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ህጋዊ ተግባራትን ያከናውናል፤

## የማዕከሉ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

### የማዕከሉ አደረጃጀት

11. ማዕከሉ የሚመራው በቦርድ ሲሆን፣ በቦርዱ የሚመረጥ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና አንድ ም/ዋና ዳይሬክተር አሉት፡፡ ተጠሪነታቸው ለም/ዋና ዳይሬክተር የሆኑ የአካዳሚክ ምርምር ዲን፣ የአስተዳደር ልማት ዲን፣ የዕቅድ ክትትል እና ግምገማ ዳይሬክቶሬት እና የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት እና ሌሎች የተለያዩ ክፍሎች በስሩ አሉት፡፡

### የማዕከሉ የሰው ኃይል

12. ማዕከሉ 192 የስራ መደቦች በመዋቅሩ የተፈቀዱለት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 142 የስራ መደቦች በሰው ኃይል ሲሸፈኑ ሃምሳ/50/ ክፍት የሥራ መደቦች ናቸው፡፡ በሰው ኃይል ከተሸፈኑት 142 የስራ መደቦች ውስጥ ሃምሳ ሁለቱ /52/ ሴቶች ሲሆኑ ዘጠና/90/ ወንዶች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በትምህርት ደረጃቸው ሲዘረዘሩ ሃያ አንድ/21/ ማስተርስ፣ አርባ ስምንት/48/ ዲግሪ፣ ሃያ ሶስት/23/ ዲፕሎማ፣ ሁለት/2/ 10+3፣ አስር/10/ 10+2፣ አንድ/1/ ሌቭል 2፣ ሁለት/2/ ሌቭል 3፣ ሶሰት/3/ ሌቭል 4፣ ሁለት/2/ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ፣ አንድ/1/ 9ኛ ክፍል እና ሃያ ዘጠኝ/29/ የቀለም ትምህርት ያጠናቀቁ ሰራተኞች ናቸው፡፡

### የማዕከሉ የፋይናንስ ምንጭ

13. ማዕከሉ ስራውን የሚያከናውነው ከመንግስት ከሚመደብለት ዓመታዊ በጀት፣ ከማታ ትምህርት እና ከሚሰጠው አጫጭር የስልጠና ለአገልግሎት ከሚያስከፍለው ክፍያ ሲሆን፣ ከ2003-2005 በጀት ዓመታት ያለው የማዕከሉ ገቢና ወጪ ከዚህ በታች በሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| የገቢ ዓይነት | በጀት ዓመት | የተስተካከለገቢ | ስራ ላይ የዋለ | ከወጭ ቀሪ |
|---|---|---|---|---|
| መደበኛ | 2003 | 5,811,408.10 | 5,787,680.92 | 23,727.18 |
| | 2004 | 10,096,393.78 | 8,412,090.88 | 1,684,302.90 |
| | 2005 | 15,504,384.79 | 11,539,546.49 | 3,964,838.30 |
| ካፒታል | 2003 | 12,600,000.00 | 956,659.81 | 11,643,340.19 |
| | 2004 | 30,000,000.00 | --- | 30,000,000.00 |
| | 2005 | 5,000,000.00 | 502,598.70 | 4,497,401.30 |
| ከውስጥ ገቢ | 2003 | 2,044,300.00 | 1,025,191.77 | 1,019,108.23 |
| | 2004 | 2,741,200.00 | 1,912,825.46 | 828,374.54 |
| | 2005 | 2,344,000.00 | 1,620,672.83 | 723,327.17 |

## ማዕከሉ የተቀበላቸው እና ያስመረቃቸው ተማሪዎች ብዛት

14. ማዕከሉ ከ2003-2005 ዓ.ም ድረስ በመደበኛ እና በማታ ክፍለ ጊዜ የተቀበላቸው ተማሪዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው 146፣ 543 እና 945 ሲሆኑ በየዓመቱ ትምህርታቸውን አጠናቀው የተመረቁ ተማሪዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው 132፣ 468 እና 834 ናቸው፡፡

## የኦዲቱ አላማ

15. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ማዕከል የተለያዩ ስልጠናዎች ለመስጠት የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን መገምገም እና በገነት ሆቴል ሊገነባ የታሰበው ሞዴል ሆቴል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እየተከናወነ መሆኑን ማጣራት ሲሆን በእነዚህ ዙሪያ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ችግሮቹን ወይም የአሰራር ግድፈቶችን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን (Recommendations) ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ማዕከል ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን ማጣራት/መገምገም/ የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

17. ከላይ በተገለጸው የኢዲት አካባቢ ሥር ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነሱም፡-
    1. ማሰልጠኛ ማዕከሉ የሚሰጣቸውን ስልጠናዎች በብቃት ለማከናወን የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን ማረጋገጥ፣
    2. በማዕከሉ ሊገነባ የታሰበው የሞዴል ሆቴል ስራ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን ማረጋገጥ፤
    3. ማዕከሉ ከክልሎች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርዓት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፤

    የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት

18. ከላይ የተመረጡት ሶስት የኦዲት ጭብጦች (audit issues) ለመመዘን የሚያስችሉ 28 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት ማዕከሉ የተቋቋመበት አዋጅ፣ ደንቦችና መመሪያዎች፣ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሰነድ እና መልካም ተሞክሮዎች ሲሆኑ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ስራው ለሚመለከታቸው የማዕከሉ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተልኮላቸዋል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) **በአባሪ 1** ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

19. ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2003 እስከ 2005 በጀት ዓመት ድረስ ማሰልጠኛ ማዕከሉ የሰጣቸው አገልግሎቶችን የስራ ክንውንን እንዲሁም በማዕከሉ ሊገነባ የታሰበው የሞዴል ሆቴል ስራን ግንባታን እና የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማስተማሪያ ክፍል መቀየር የሥራ አፈጻጸምን ይመለከታል፡፡
20. ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የማዕከሉ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች፣ ለዲፖርትመንት ኃላፊዎች፣ ለአካዳሚክ ዲን፣ ለገነት ሆቴል ስራ አስኪያጅ፣ ለማዕከሉ ም/ዳይሬክተር እና ስራውን ጀምሮ ለነበረው ለሳሙኤል ሳ/ማርያም ተቋራጭ ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እና በናሙና ለተመረጡ የማዕከሉ ተማሪዎች (ለ63 ተማሪዎች) መጠይቅ በማስሞላት ሲሆን በተጨማሪ የተግባር ልምምድ በሚያደርጉበት ወቅት (በአካል በመገኘት) ነው፡፡

## መደበኛ/የቀን/ ስልጠና የሥራ ሂደት መግለጫ (System description)

21. መደበኛ የሥልጠና የሥራ ሂደት የአሰራር ስርዓት ከወቅቱን ካሪኩለም ፈትሾ ከማፅደቅ፣ የመግቢያ መስፈርት ማዘጋጀትና ማፅደቅ፣ የምልመላ መመሪያ ማዘጋጀትና መመሪያ ማዘጋጀትና ማፅደቅ፣ ፈተና ማዘጋጀት ማባዛት፣ ማደራጀትና ለፈታኞች ማስረከብ፣ ስለምልመላ ለክልል ቢሮዎችና ለተወዳዳሪዎች ማሳወቅ፣ አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት መልማዮች ማሰማራት፣ የመመዝገቢያና የመፈተኛ ቦታ በማዘጋጀት ተወዳዳሪዎችን መመዝገብና ፈተና እና ቃለ መጠይቅ መስጠት ያለፉ ተማሪዎችን በመቀበል ትምህርት ማስቀጠል የሚል ሂደቶች ያካተተ ነው፡፡

## ተከታታይ/ የማታ/ ስልጠና የሥራ ሂደት መግለጫ

22. ተከታታይ/የማታ/ ስልጠና የሥራ ሂደት መግለጫ የስልጠና መስክ ከመወሰን በመጀመር የመግቢያ መስፈርት መወሰን፣ ማስታወቂያ ማውጣት፣ ምዝገባ ማካሄድ፣ የመግቢያ ፈተና ማዘጋጀት፣ የቃልና የጽሁፍ ፈተና መስጠት፣ ውጤት ማሳወቅ፣ ያለፉትን መቀበልና ኦሬንቴሽን መስጠት፣ ፕሮግራም ማውጣትና ስልጠናውን በንድፈ ሃሳብ፣ በተግባርና በቤተሙከራ መስጠት፣ የተርምና ተከታታይ ምዘና ማካሄድ፣ ፈተናውን በማረም ውጤቱን ለተማሪዎች ማሳወቅ፣ ውጤት ማሰባሰብና ማጠናቀር ለሬጅስትራር መስጠት፣ ተማሪዎች ካላለፉ ማሰናበት ካለፉ ቀጣዩን ስልጠና በንድፈ ሃሳብ፣ በተግባር፣ በቤተሙከራ ማካሄድ በቱሪስት አገልግሎት ተቋማት በስራ ላይ ልምምድ ማሰማራት፣ የተርምና ተከታታይ ምዘና ማካሄድ፣ በተቋማት በመገኘት ክትትልና ቁጥጥር ማካሄድ፣ ተግባራዊ ልምምድ ካላጠናቀቁ እንዲያጠናቅቁ ማሰማራት ካጠናቀቁ ውጤቱን ማሰባሰብና ማጠናቀር ለሬጅስትራር ማቅረብ፣ የመማር ማስተማሩን ሂደት መገምገም፣ በኢንዱስትሪው ለተግባር ልምምድ ማመቻቸትና መላክ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ ተግባራዊ ልምምድ ማጠናቀቅ፣ ውጤት ማሰባሰብ ሮስተር ማጠናቀርና ሮስተር ለሬጅስትራር ማቅረብ፣ አጠቃላይ ውጤታቸውን ለአካዳሚክ ኮሚቴ ማቅረብ፣ ሰልጣኞች የመመረቂያ መስፈርት ካሟሉ ተመራቂ ተማሪዎችን ማሳወቅ የትምህርት ማስረጃና ሽልማት በማዘጋጀት ማስመረቅ የሚሉ ሂደቶችን ያካተተ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## የስትራቴጂክ ዕቅድ እና ዓመታዊ ዕቅዶች የሚዘጋጁ እና በዕቅዱ መሰረት መስራቱን በተመለከተ፣

23. ማዕከሉ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያዘጋጅና በስትራቴጂክ ዕቅዱ የተመነዘረ ዓመታዊ ዕቅዶችን በማዘጋጀት በዕቅድ የተያዙ ስራዎችን ሊተገብርና በስራ አፈፃፀሙ የታዩ ችግሮችን በመለየትና እርምጃ በመውሰድ ሊያስወግድ ወይም እንዲቀንስ ማድረግ አለበት፡፡

24. የባህልና ቱሪዝም ሚ/ር በስሩ ያሉ መ/ቤቶችን በማካተት ባዘጋጀው የ5 ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድን መሠረት በማድረግ ማዕከሉ የራሱን የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ (ከ2003— 2007በጀት ዓመት) ያላዘጋጀ መሆኑ፣ በማዕከሉ የ2003 እና የ2004 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣ እንዲሁም በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ መረጃዎች በግልፅ/በቁጥር፣ በፐርሰንት/ በሚያሳይ መልኩ ያልተቀመጡ መሆኑ፣ አዲስ የሚገቡ ተማሪዎች የመቀበል አቅሙ እየጨመረ የሄደ ቢሆንም ከ2003-2006 በጀት ዓመት የተቀበለው የተማሪ ቁጥር እንደ ቅደም ተከተላቸው 146፣ 543፣ 945 እና 1,023 ሲሆን በአጠቃላይ 2,657 ተማሪዎች በመሆኑ በእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ(GTP) መጨረሻ ላይ በ2007 በጀት ዓመት የተማሪዎች የመቀበል አቅም 11,070 ይደርሳል ተብሎ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን በፊት ከነበረው አፈፃፀም ጋር ሲታይ የተያዘው ዕቅድ የተጋነነ መሆኑን ከቃለ መጠይቅ እና ከእቅድ ሰነድ እና አፈጻጸም ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

25. ስለሁኔታው የዕቅድ ክትትልና እና ግምገማ ዳይሬክተሩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የተቀጠሩት በ2004 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ መሆኑ፣ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ በቢ.ኤስ.ሲ(BSC) ውስጥ ተካቶ የተሰራና የ2003 እና የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድን ለተሞክሮ በሚፈለግበት ወቅት ያልተገኘ መሆኑን እና ዳይሬክቶሬቱ ራሱ የተከፈተው በ2004 ዓ.ም መሆኑን እና በፊት ስራው በሌላ ክፍል ተደርቦ የሚሰራ የነበረ በመሆኑ ስራዎች በተጠናከረ መልኩ ያልተሰሩና ግልፅ የሆነ መረጃ እንዳይያዝ የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

26. እንዲሁም ም/ዋና ዳይሬክተሩ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ በጀት ዓመት ዕቅድ እና የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ መኖሩን ቢገልጹም ማስረጃውን ግን ማቅረብ አልቻሉም፡፡ የ2003 በጀት ዓመት ዕቅድ ሊኖር እንደሚችል

እና ግን አለመገኘቱን በመግለፅ ዕቅዶቹ ያልተገኙበት ምክንያት የዕቅድ ክትትል እና ግምገማ ዳይሬክቶሬቱ የተቋቋመው በ2004 ዓ.ም. በመሆኑ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች አፃፃፍ ግልፅነትና ሙሉ መረጃዎች አለመያዝን በተመለከተ ችግሩ የአደረጃጀትና የአቅም ማነስ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

27. በመሆኑም በኦዲቱ ወቅት እንደታየው የ2005 እና የ2006 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ የተዘጋጀ መሆኑ የሚያበረታታ ቢሆንም አንድ ተቋም ከስራዎች ሁሉ ማስቀደም ያለበት ዕቅድ በማዘጋጀት በዕቅዱ መሠረት ስራዎችን ማከናወን ሲሆን ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በስሩ ያሉ መ/ቤቶችን አካቶ ባዘጋጀው የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ (ከ2003-2007 በጀት ዓመት) መሠረት በማድረግ ማዕከሉ የራሱን የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ እና ዓመታዊ ዕቅድ አለመዘጋጀቱ፤ በየዓመቱ የተከናወኑ ስራዎችን በዕቅዱ መሠረት የተከናወኑ ስለመሆኑ፣ ለመከታተልና ለመቆጣጠር እንዲሁም ለመለካት የማያስችል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

## <u>በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ብቁና የሰለጠነ የሰው ኃይል ከማፍራትና ስልጠናው በተጠናከረ ሁኔታ እንዲሰጥ የሚያስፈልጉ ሞጅሎች ስለመኖራቸው</u>

28. በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚሰጡ ስልጠናዎችን ከማጠናከርና ብቁና የሰለጠነ የሰው ኃይል ከማፍራት አኳያ በቤተ መጻህፍትም ሆነ ለተማሪዎች የሚደርሱ የተለያዩ የስልጠና ሞጅሎችን በመግዛትም ሆነ በማዕከሉ በማዘጋጀትና በማባዛት ስልጠናውን በተጠናከረ ሁኔታ ሊሰጥ ይገባል፡፡

29. ይሁን እንጂ  በቤተመጽሐፍቱም የቅርብ ጊዜ (ወቅታዊ የሆኑ መጽሃፍት) የሌሉ መሆኑ፣ መጽሃፍትን ተማሪዎች ተውሰው ወስደው ስልጠናቸውን የሚያጠናክሩበትና የቤት ስራዎቻቸውን የሚሰሩበት ሁኔታ ያልተመቻቸ መሆኑ፣ በ2006 ዓ.ም ወደ 27 የሚሆኑ ሞጅሎች ታትመው/ተባዝተው/ በቤተመጽሐፍት የተቀመጡ ቢሆንም በተማሪዎች ወጪ ተደርገው አገልግሎት አለመዋላቸው፣ በቤተመጽሐፍቱ ውስጥ ለተማሪዎች ከመፃህፍት ያጡትን መረጃ እና ተጨማሪ ዕውቀት እንዲያገኙ ሊያስችላቸው የሚያስችል የኢንተርኔት አገልግሎት ያልተዘረጋ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት በተደረገ የመስክ ምልከታ እና እንዲሁም ከዲፐርትመንት ኃላፊዎች ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

30. ይህን በተመለከተ የቤተ መጽሃፍቱ (ላይብረሪ) ኃላፊው ተጠይቀው ለሆቴልና ቱሪዝም ስልጠና የሚያገለግሉ መፃህፍትን በገበያ ላይ ማግኘት በጣም አስቸጋሪ እንደሆነና ተማሪዎች ከመሀል የሚፈልጓቸውን ገጾች እየቀደዱ በመውሰድ የሚያጎድሏቸው በመሆኑ፣ መጻህፍትን ለመግዛት ኘሮፎርማ ተሰብስቦ እስኪገዛ ያለው ጊዜ ረዥም

በመሆኑ ተጠናቆ መጻህፍቱን ለመግዛት በሚኬድበት ጊዜ መጽሀፍቶቹ በገበያው ላይ የሚጠፋበት ሁኔታ መኖሩን ገልጸዋል፡፡፣ አሁን በቤተመጻህፍቱ ያሉት መጻህፍት ካለው የተማሪ ቁጥር ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ከመሆኑ በተጨማሪ የቦታ ጥበት መኖሩ እንዲሁም የኢንተርኔት አገልግሎት በቤተመጻህፍቱ የሌለ በመሆኑ ተማሪዎች ተጨማሪ መረጃ እንዳያገኙ ያደረገ መሆኑን ገልጸው ችግሩ በማዕከሉና በቤተ መጽሃፍቱ መካከል ርቀት በመኖሩ ሲሆን ወደፊት መስመሩን ለመዘርጋት እና ቤተ መጽሃፍቱ ከስራ ሰዓት ውጪ እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓትና ቅዳሜን ለመስራት በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

31. የሆቴልና ቱሪዝም ዲፓርትመንት ኃላፊዎች እንደገለፁት የመማሪያ ሞጅሎች አለመዘጋጀት የፋይናንስ እጥረት ምክንያት መሆኑን የገለጹ ሲሆን ኦዲቱ በተዳሰሰበት ከ2003-2005 ወቅት በስፋት እንደማይዘጋጁ ነገር ግን በ2006 ዓ.ም መምህራኖችን ግፊት በማድረግና በማበረታታት ማንዋል እንዲያዘጋጁና በ30 ኮፒ እየተባዛ ቤተ መጻህፍት እንዲቀመጥ የተደረጉ መሆኑን የገለጹ ሲሆን ለአጫጭር ስልጠናዎች ወጥ የሆነ ማንዋሎች የሌሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

32. የአካዳሚክ ዲኑ ይህን በተመለከተ ተጠይቀው ሲመልሱ ከዚህ በፊት ትኩረት የሚሰጠው ለአስተዳደሩ ሲሆን አሁን ለአካዳሚኩ ትኩረት እየተሰጠው በመሆኑ በ2006 ዓ.ም የመማሪያ ሞጅሎች ተዘጋጅተው በቤተ መጻህፍት እና በየትምህርት ክፍሉ እንደሚገኙ የገለፁ ሲሆን የኢንተርኔት አገልግሎት በላይብረሪ እንዲዘረጋ ብዙ ጊዜ ያሳሰቡ መሆናቸውን ነገር ግን ለአካዳሚኩ የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ በመሆኑ በመምህራን ማረፊያ ክፍል እንኳን ባለመዘርጋቱ መምህራኑ መፈለግ ያለባቸውን መረጃ ማግኘት እንዳይችሉ እንዳደረጋቸው ገልፀዋል፡፡

33. ምክትል ዋና ዳይሬክተሩም ስለሁኔታው ሲገልጹ በቤተ መጽሃፍት (በላይብረሪ) የኢንተርኔት አገልግሎት ያልተዘረጋበት ምክንያትሲገልጹ ከዋናው ግቢ እስከ ገነት ሆቴል ድረስ ለመዘርጋት ብዙ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑን እና ይህም አዋጭ ሆኖ አለመሆኑን እና አገልግሎቱን የሚሹ ሰልጣኞች በዋና ግቢ በሚገኘው ICT ማዕከል እንዲጠቀሙ እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

34. ይሁን እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ለተማሪዎች የሚሆኑ 27 ሞጅሎች እንደ አስፈላጊነታቸው አስራ ስድስት ሞጅሎች በአምስት/5/፣ አምስት ሞጅሎች በአስር/10/ ኮፒ እና ሌሎቹ በሶስት እና በአራት ኮፒ እየተባዙ እንደተቀመጡ እና ቤተመጻህፍቱም እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓት በተጨማሪ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ

መስራት እንደጀመረ የገለፁ ሲሆን የኦዲት ቡድኑም በቤተመጻህፍቱ በመገኘት አረጋግጧል፡፡

35. ምንም እንኳን በ2006 ዓ.ም የተወሰኑ የመማሪያ ሞጅሎችን በማባዛት በላይብረሪ እንዲቀመጡ የተደረገ መሆኑ የሚያበረታታ ቢሆንም ለተማሪዎች የሚያስፈልጉ ወቅታዊ መጽሐፎች፣ መጽሄቶች፣ ወቅታዊ ጉዳዮችን የሚያውቁበት የተለያዩ ጋዜጦች እና ከመጽሐፍ የማይገኙ እና የተለያዩ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት የሚረዳቸውን የኢንተርኔት አገልግሎት በቤተመጻህፍቱ አለመኖር ተማሪዎች ማግኘት የሚገባቸውን እውቀት ሳያገኙ እንዲቀሩ እየዳረገ እንደሚገኝ ማዕከሉ ሊገነዘብ ይገባል፡፡

## ለተማሪዎች ስልጠና የሚሰጥበት እና የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት መሳሪያዎች የተሟሉ መሆናቸውን በተመለከተ

36. ተማሪዎች ስልጠና በሚወስዱበት ጊዜም ሆነ የተግባር ልምምድ በሚያደርጉበት ወቅት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ሊሟሉ ይገባል፡፡

37. በኦዲቱ ወቅት ተማሪዎች ስልጠና ከወሰዱ በኋላ የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት ክፍሎች ውስጥ የተግባር መለማመጃ ማሽኖች በአብዛኞቹ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ ለምሳሌ በምግብ ዝግጅት የተግባር ክፍል/ኪችን/ ውስጥ ካሉት የተግባር መለማመጃ ማሽኖች ውስጥ ሰባት (7) ማሽኖች (dry food storage area, perseble food storage area እና ሌሎች አምስቶች የመሳሰሉት) የተበላሹ እና አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑን፣ አብዛኞቹ ማሽኖች ተቋሙ ሲመሰረት /ከ40 ዓመታት በፊት/ ጀምሮ የነበሩ መሆናቸውና በወቅቱ የነበረው የተማሪዎች ቁጥር 70 እና 90 ሲሆን በ2005 ዓ.ም ከተቀበለው የተማሪ ብዛት 945 ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ በጣም ሰፊ መሆኑን የተማሪው ቁጥር ሲጨምር የማሽኖች ቁጥር ያልጨመረ መሆኑ፤ እንዲሁም አሁን ያሉት ማሽኖችም በከፊል ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡ /ሲንኩ የሚያፈስ፣ ውሃ ማሞቂያው የማይሰራ፣ የጋዝ ምድጃው የሚያፈስ፣ ባኔማሪዬ /የምግብ ማቆያ/ ወርሚንግ ቴብል፣ የማቀዝቀዛ ክፍሉ.... / መኖራቸው በተጨማሪ ተማሪዎች የምግብ ማብሰል በኪችን የተግባር ልምምድ ካደረጉ በኋላ የሚታጠቡበት መታጠቢያ እና ልብስ መቀየሪያ ክፍል የሌላቸው መሆኑን እና የመስተንግዶ ስልጠና የሚያደርጉበት ክፍል ወንበሮች የተለያዩ ቅርጽ ያላቸው መሆኑን በመስክ ምልከታ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

38. እንዲሁም በዋናው ግቢ ለሚማሩ ተማሪዎች ተብሎ የተሰራ መጸዳጃ ክፍል የሌለ ሲሆን በገነት ሆቴል ለሚማሩ ተማሪዎች አራት መጸዳጃ ክፍሎች ቢኖሩም ንፅህና የሌላቸው መሆናቸውን፣ ማዕከሉ ሁለት መምህራንን በአየር መንገድ የቲኬቲንግ ስልጠና ቢወስዱም ስልጠናውን በተግባር ለማዋል የሚያስችል ሶፍትዌር ባለመኖሩ የተግባሩን ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚሰጥ ንድፈ ሃሳብ ብቻ አሰልጥነው እንዲወጡ ማድረጉ እና የማሰልጠኛ ኮምፒውተሮች የተገዙ ቢሆንም አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆኑን በመስክ ጉብኝት ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡




ፎቶ 1 የምግብ ዝግጅት ተማሪዎች የተግባር ልምምድ በሚያደርጉበት ክፍል ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡ መሳሪያዎች

39. ስለሁኔታው የሆቴል ዲፓርትመንት ክፍል ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የተግባር መማሪያ ሾፖች/ክፍሎች/ እስከ 2003 ዓ.ም ያልነበሩና በ2004 ዓ.ም የተጀመሩ መሆኑን የምግብ ዝግጅት እና የመስተንግዶ፤ እንዲሁም በ2005 ዓ.ም የሀውስ ኪፒንግ የተግባር መማሪያ ሾፖች/ክፍሎች/ መኖራቸው እና የተግባር መማሪያ ዕቃዎቹ እንዳረጁና አንዳንዶቹም እንደሌሉ እና ለበላይ ሃላፊዎች ተጠይቆ መልስ እንዳልተሰጠበት ገልጸዋል፡፡በተጨማሪም በየወቅቱ የሚከለሰው የትምህርት ካሪኩለም ችግር እየፈጠረብን ይገኛል በማለት ገልፀዋል፡፡

40. ይህን በተመለከተ የቱሪዝም ክፍል ኃላፊ ተጠይቀው ሲመልሱ በዚህ ዓመት/2006/ የተግባር መለማመጃ ክፍል ለማደራጀት እና ኢ-ማርኬቲንግ ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል ሶፍት ዌር ለመግዛት በጥረት ላይ መሆናቸውንና አሁን ስልጠና በመስጠት ላይ ያሉ መምህራን በቲዎሪ ብቻ ለተማሪዎች ስልጠና እየሰጡ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

41. የአካዳሚክ ዲኑ ይህን በተመለከተ ሲያስረዱ ማሰልጠኛ ተቋሙ በአብዛኛው ትኩረት የሚያደርገው አስተዳደራዊ ሥራ ላይ እንጂ አካዳሚክ/ትምህርት/ ክፍሉ ላይ ትኩረት

ባለመሰጠቱ በተለይ ለትምህርት ግብዓት የሚውሉ ቁሳቁሶች ግዢ ላይ የተባባሰ ችግር እንዳለ ገልጸዋል፡፡

42. ም/ዋና ዳይሬክተሩ የተግባር ማሰልጠኛ ማቴሪያሎች ያለመሟላትን በተመለከተ ሲመልሱ ሰልጣኞች የተግባር ልምምድ የሚያደርጉት ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በሚፈጠር ትስስር መሆኑን በስልጠና ስትራቴጂው ተገልጾአል፡፡ ይሁንና ይህን ከማጠናከር አንፃር በተቋሙ ውስጥ የተግባር ማስተማሪያ ክፍሎች በማደራጀት ግብዓት (ማቴሪያሎች) ጊዜውን ጠብቆ እየተሟሉ የሚገኙ ሲሆን ያልተሟሉ ማቴሪያሎችም በሂደት ይሟላሉ፡፡ ያልተሟሉበት ምክንያት ማዕከሉ ድሮ ይሰራበት የነበረው አሰራር ማለትም የቁጥቁጥና የለቀማ ግዢ ለክራይ ሰብሳቢነት የተጋለጠ በመሆኑ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከ2005 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ ቀልጣፋና ውጤታማ አሰራር ተግባራዊ እየሆነ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

43. ይሁን እንጂ ሁሉም በሰጡት ምላሽ ላይ ግብዓቶች(ማቴሪያሎች) አለመሟላታቸውን የገለጹ ሲሆን ለዚህ ዋና የችግሩ መንስኤ ተቋሙ በዕቅድ ያለመመራቱን እና ቅንጅታዊ አሠራር ባለመኖሩ ምክንያት የተከሰተ ችግር መሆኑን ነው ለመረዳት የተቻለው፡፡ በመሆኑም ማዕከሉ ዋና ዓላማው የሆነውን በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ስልጠና በመስጠት ብቁና ተወዳዳሪ የሆኑ ባለሙያዎችን የማፍራት ተግባር ከግብ ለማድረስ በስልጠናም ሆነ በተግባር ልምምድ ወቅት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች አለመሟላት በትምህርት ጥራቱ ላይ አሉታዊ አስተዋጽኦ የሚፈጥሩ መሆናቸው ሊታመንበት እንደሚገባ ማዕከሉ ሊገነዘብ ይገባል፡፡

## <u>ችግር ፈቺ የሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎች የተከናወኑ መሆኑን በተመለከተ</u>

44. ማእከሉ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ዕድገትና ልማት ጠቃሚና ችግር ፈች የሆኑ የተለያዩ ጥናትና ምርምር ሊያከናውን እና ለሚመለከታቸው አካላት ሊያስተላለፍ ይገባል፡፡

45. ይሁን እንጂ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ስትራቴጂክ ዕቅድ/ከ2003-2007/ እና ማዕከሉ በ2005 ዓ ዓመታዊ ዕቅድ ላይ አስር የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማጥናትና በማሳተም ለሚመለከተው አካል/ለባለድርሻ/ ማስተላለፍ በሚል በእቅድ የተያዘ ቢሆንም የጥናትና ምርምር ስራዎች ያልተከናወኑ መሆኑን፤ እንዲሁም በሽራተን አዲስ በ2004 እና በ2005 ዓ.ም ከተለያዩ ዩኒቨርስቲ ከተውጣጡ ባለሙያዎች በሆቴሎችና በቱሪዝም ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ የተጠኑ ጥናቶች ቢቀርቡም ማዕከሉ የተገኙ ችግሮችን እና ጠቃሚ ተሞክሮችን በማዘጋጀትና በማሳተም ለባለድርሻ አካላት ያላሰራጨ መሆኑን ከዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. ስለሁኔታው የጥናትና ምርምር ክፍል ኦፊሰር ተጠይቀው ሲገልጹ ክፍሉ የተቋቋመው እና የሰው ኃይሉም የተቀጠረው በ2005 ዓ.ም. አጋማሽ በመሆኑ፣ ክፍሉ ከተቋቋመ በኋላ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች/ማቴሪያሎች/ እስኪሟሉ፣ በቅድሚያ ጥናትና ምርምርን ለማከናወን መመሪያ መዘጋጀት ስለነበረበት እና ለጥናትና ምርምሩ ትኩረት ባለመሰጠቱ ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

47. የማዕከሉ አካዳሚክ ዲን የጥናትና ምርምር ስራን በተመለከተ ምንም የጥናትና ምርምር ስራዎች ያልተሰሩና በማዕከሉ ያሉ ችግሮች ተለይተው ያልቀረቡላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

48. ም/ዋና ዳይሬክተሩ ይህን በተመለከተ ሲገልጹ የክፍሉን የስራ እንቅስቃሴ ውጤታማ የማድረግ ችግር እንዳለ በየደረጃው የገመገሙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

49. ሆኖም የማሰልጠኛ ተቋሙ ዋና ተልዕኮ የሆነውን የጥናትና ምርምር ስራን አለማከናወኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ማዕከሉ በዕቅድ የያዘውን የጥናትና ምርምር ስራዎች አለመሰራታቸው በሆቴልና ቱሪዝም ላይ የሚታዩ ችግሮች ጐልተው እንዳይወጡና ችግሮቹ መፍትሄ እንዳያገኙ የሚያደርግ፣ ባለድርሻ አካላት ከጥናቱ መገንዘብ የሚገባቸውን ችግሮች ተረድተው እንዳይፈቱ የሚያደርግ፣ ጥናቶች ተጠንተውና ታትመው በላይብረሪ ባለመቀመጣቸው ሌሎች ጥናት አድራጊዎች ወይም ተማሪዎች ከጥናቱ መውሰድ የሚገባቸውን ተሞክሮና ዕውቀት እንዳይወስዱ እያደረገ ይገኛል፡፡

## <u>ለተማሪዎች በስልጠና ወቅት የክፍል ጊዜ ብክነት እንዳይኖርና የስልጠና አሰጣጥ ሂደትን መቆጣጠሪያ ስርዓት የተዘረጋ ስለመሆኑ፣</u>

50. በማዕከሉ የሚሰጡ ስልጠናዎች ላይ የክፍለ ጊዜ ብክነት እንዳይኖር እና ተማሪዎች ለተግባር ልምምድ ወደ ተለያዩ የሆቴልም ሆነ የቱሪስት አገልግሎት መስጫ ተቋም በሚሄዱበት ወቅት ማዕከሉ የስልጠና ሂደቱንም ሆነ የተግባር ልምምዱን ክትትልም ሆነ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችለው ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

51. ሆኖም ለተማሪዎች ስልጠና የሚሰጠው በዋና ማዕከሉ ግቢ በሚገኙ ሁለት (2) የቲዎሪ መስጫ ክፍሎች እና በገነት ሆቴል ግቢ በሚገኙ በጊዜያዊነት በቆርቆሮ በተሰሩ ስምንት(8) ክፍሎች እና የሆቴልም ሆነ የቱሪዝም ተማሪዎች የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት አራት(4) ክፍሎች ናቸው፡፡ በገነት ሆቴል በሚገኙ ስምንት/8/ ክፍሎች ከዋናው ግቢ የሚርቁ በመሆናቸው በእነዚህ ክፍሎች አስተማሪዎች በሚቀሩበት ጊዜ በግቢው መከታተያ እና መቆጣጠሪያ ስርዓት አለመዘርጋቱን እና ተማሪዎችም የክፍለ ጊዜ ብክነት እያጋጠማቸው ተገቢውን ስልጠና የማያገኙ መሆኑን

በናሙና ተመርጠው መጠይቅ ከሞሉ ተማሪዎች እና መጠይቅ ከቀረበላቸው የዲፖርትመንት ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

52. በማዕከሉ የንድፈ ሃሳብ ስልጠና ሰላሳ በመቶ (30%) የተግባር ልምምድ ሰባ በመቶ (70%) ድርሻ የሚይዝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የተግባር ልምምድ ለማድረግ  በተለያዩ ሆቴሎችና የቱሪዝም አገልግሎት መስጫ ተቋማት በሚሄዱበት ጊዜ የተግባር ልምምዱ በሚፈለገው ደረጃ እየተከናወነ ስለመሆኑ የክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት በማዕከሉ ያልተዘረጋ መሆኑን፣ እንዲሁም በልምምዱ ወቅት ለሚያጋጥማቸውም ችግር ድጋፍ የማያገኙ መሆኑን እና የተግባር ልምምዱን በብቃት ሳያከናውኑ እንደሚጨርሱ በናሙና ተመርጠው መጠይቅ ከሞሉ ተማሪዎች እና መጠይቅ ከቀረበላቸው የዲፖርትመንት ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

53. ስለሁኔታው የሆቴል ዲፖርትመንት ኃላፊ ተጠይቀው ሲመልሱ መምህራን በራሳቸው በሚገጥማቸው ችግር ምክንያት ሊቀሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ያባከኑትን ክፍለ ጊዜ በማሽጋሸግ እንዲሰጡ ይደረጋል ሆኖም እራሱን የቻለ ተቆጣጣሪ የለም፡፡ ነገር ግን በራሳችን ይህን ችግር ለመቅረፍ በዲፖርትመንቱ ያሉትን የሰው ኃይል በቀኖች በመከፋፈል የመቆጣጠር ስራ ይሰራል በማለት የገለፁ ሲሆን በተግባር ልምምድ ወቅት ክትትልና ድጋፍ የማይደረገው ለመምህራኖቹ የሚገባቸውን የትራንስፖርትም ሆነ ሌላ ክፍያ ስለማይከፈላቸው የማይበረታቱ መሆናቸውን እና ለዲፓርትመቱ ለቁጥጥር ስራ በጀት ሲበጀትለት በአስተዳደር ሰዎች ስራ ላይ እንዳይውል ስለሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

54. የቱሪዝም ዲፖርትመንት ኃላፊ የክፍለ ጊዜ ብክነትን በተመለከተ በሰጡት ምላሽ በማዕከሉ እና ስልጠና በሚሰጥበት ቦታ ያለው ርቀት ስራውን አድካሚ ማድረጉንና ይህም በቀን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ክፍተት እንደሆነ ነገር ግን በማታው ክፍለ ጊዜ ተቆጣጣሪዎች መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በተግባር ልምምድ ወቅትም ክትትል እንደማይደረግና ይህ የሆነበት ሁኔታ የኪስ ገንዘብ ክፍያ ለአስተማሪዎቹ ስለማይከፈላቸው ይህን ስራ የማይሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

55. ስለሁኔታው የአካዳሚክ ዲኑ ተጠይቀው ሲመልሱ በመደበኛው ክፍለ ጊዜ የተለየ ተቆጣጣሪ አካል የማይመደብ መሆኑን፣ አሁን ባለው ሁኔታ የሚደረገው ከየትምህርት ክፍሉ ኃላፊዎች እና እሳቸውም እየሄዱ የሚቆጣጠሩበት ሁኔታ መኖሩንና ተማሪዎችም በዚህ ቁጥጥር ሥርዓት ውስጥ አንድ ለአምስት አደረጃጀት ስላላቸው የሳምንቱን ሁኔታ ተወካዮች ሪፖርት የሚያደርጉ መሆኑን፣ በተጨማሪ አስተማሪ ከቀረም ስልክ በመደወል የሚያሳውቁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡  በተግባር ልምምድ ወቅት

የሚደረግ ቁጥጥርን በተመለከተ ሰላሳ በመቶ(30%) በተቋሙ ሰባ በመቶ (70%) በኢንዱስትሪ ልምድ እንዲያደርጉ የሚያዝ አሰራር ቢኖርም ተቋሙ ደጋፊ ትምህርቶችን (common course) የሚሰጥ በመሆኑ፣ የተግባር ላይ ልምምዱ በዓመቱ መጨረሻ የሚደረግ በመሆኑና ወቅቱም ክረምት እና መምህራኖች ዕረፍት ላይ በመሆናቸው የሚደረገው ቁጥጥር አናሳ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

56. የማዕከሉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር የተግባር ልምምድ ክትትልን በተመለከተ ሲገልፁ ስልጠና በሁለትዮሽ ማለትም በማዕከሉና በአገልግሎት ሰጭ ተቋማት የሚሰጥ በመሆኑ ማዕከሉ የሰልጣኞች ክፍተት በመግለጽ ወደ ተቋማቱ የሚላክ ሲሆን ተቋሙም የሰልጣኞችን ክፍተት በትክክል ለመሙላት ኃላፊነት ወስዶ በመስራት ለሰልጣኞች ማረጋገጫ እንደሚሰጥ ገልፀዋል፡፡ ሰልጣኞቹ ይህንን ማረጋገጫ ካላመጡ የተግባር ስልጠና እንዳልወሰዱ የሚቆጠር መሆኑን እና እንደ ተቋም የሚከተሉት ስርዓት ይህን መሆኑን ገልፀዋል፡፡

57. በመሆኑም ማዕከሉ አብዛኛውን ስልጠና የሚሰጠው በገነት ሆቴል በሚገኙ ክፍሎች በመሆኑና አስተማሪዎች በቸልተኝነት ወይም በተለያየ ምክንያት በክፍለ ጊዜ በማይገኙበት ጊዜ ለማወቅ የሚያስችል ስርዓት አለመኖሩ ወይም የሚቆጣጠር አካል ባለመኖሩ ተማሪዎች ማግኘት የሚገባቸውን ስልጠና /ዕውቀት/ እንዳያገኙ የሚያደርግ መሆኑን እንዲሁም ተማሪዎች የተግባር ልምምድ ለማድረግ በተለያዩ ሆቴሎችም ሆነ የቱሪስት አገልግሎት መስጫ ተቋም በሚሄዱበት ጊዜ ምንም እንኳን ተማሪዎቹ ለተግባር ልምምድ በሚሄዱበት ወቅት ይዘውት የሚሄዱት ፎርም በአገልግሎት መስጫ ተቋማቱ ተሞልቶ የሚመለስ ቢሆንም ተቋማቱ ተማሪዎቹ በሚሰለጥኑበት የስልጠና ዘርፍ ላይመድቧቸው የሚችሉ መሆኑን፤ ለሰልጣኞች ትኩረት ሰጥተው ክትትል እና ድጋፍ ላያደርጉላቸው ስለሚችል፤ ማዕከሉ ተማሪዎቹ በተቋሙ በትክክል በሞያቸው መመደባቸውን፣ የተሰጣቸውን ጊዜ በትክክል መጠቀማቸውንና ሊደረጉ የሚገቡ ድጋፎችን ሳይደረጉ መቅረቱን መከታተያ ስርዓት አለመዘርጋቱ ሰባ በመቶ የሚሆነውን የተግባር ልምምዱን ተማሪዎች በተሰጣቸው ጊዜ ማግኘትና ማወቅ የሚገባቸውን የተግባር ልምምድ እንዳያገኙ ሊያደርግ እንደሚችል ሊታወቅ ይገባል፡፡

## <u>በማዕከሉ ለተማሪዎች የሚሰጥ የኪስ ገንዘብ በወቅቱ የሚደርሳቸው ስለመሆኑ</u>

58. በማዕከሉ በመደበኛ ክፍለ ጊዜ ለሚማሩ ተማሪዎች በመንግስት የሚሰጠው የኪስ ገንዘብ በወቅቱ ሊደርሳቸውና ለሌሎች የመንግስት ተቋማት ተጨማሪ የተደረገውን ብር 90 ለማዕከሉ ተማሪዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡

59. ሆኖም በማዕከሉ ለሚማሩ መደበኛ ተማሪዎች ለአንድ ተማሪ የሚሰጠው የኪስ ገንዘብ በወር ብር 330 ሲሆን መንግስት ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ለሌሎች የትምህርት ተቋማት ተጨማሪ በማድረግ ወደ ብር 420 ያደገ ሲሆን ለተቋሙ ተማሪዎች ግን ይህንን መሠረት በማድረግ ያልተጨመረ መሆኑ፣ የሚሰጠው የኪስ ገንዘብም በወቅቱ የማይደርሳቸው መሆኑን ይህም በአብዛኛው በማዕከሉ የሚማሩ ተማሪዎች ከክልል የሚመጡና ማዕከሉ ማደሪያ ክፍል የማይሰጣቸው በመሆኑ ከቤት ኪራይ ጀምሮ ያለውን ወጪ የማይሸፍን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ኑሮን ከባድ ያደረገውና ለመማር አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ይህንንም ለመሸፈን ቤት የሚቀንስበት በመፈለግ ራቅ ያለ አካባቢ ስንሄድ ማዕከሉ የሚገኘው መሃል ከተማ በመሆኑ ለትራንስፖርት እንግልት መዳረግ፣ ሴቶች እራሳቸውን ለአደጋ የሚያጋልጥ ስራ መስራት፣ በትርፍ ሰዓት ስራ ለመስራት ሲታሰብ ከትምህርት ጋር በመጋጨት ትምህርቱን ትኩረት ሰጥቶ ለመማር አለመቻል ለመሳሰሉት ችግሮች ያጋለጣቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

60. በመሆኑም የሆቴል ዲፓርትመንት ኃላፊ ይህን በተመለከተ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ የመምህራን የመቆጣጠሪያ ሊስት ወደ ዲፓርትመንቱ ቶሎ ባለመድረሱ በዚህ ምክንያት ወደ ፋይናንስ አንድ ወይም ሁለት ቀን በመዘግየት ቢሄድም ፋይናንስ ክፍል በቶሎ በመስራት አይከፈልም፡፡ የኪስ ገንዘብ በሰዓቱ ባለመከፈሉ አንዳንድ ተማሪዎች የመራብ ችግር እየገጠማቸው ጉዳና መውጣት እና ሴት ተማሪዎች ያላስፈላጊ ስራዎችን እንዲሰሩ እየተገደዱ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡

61. በመቀጠል የቱሪዝም ዲፓርትመንት ኃላፊ የክፍያ ማነስ እና መዘግየት ያለ ችግር መሆኑን እና የፋይናንስ የሥራ ክፍል ችግር መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ዲፓርትመንቱ በወቅቱ የተማሪዎችን ስም ዝርዝር በመግለፅ ለአካዳሚክ ዲን የሚመራ መሆኑን ነገር ግን ለምን እደሚዘገይ የማያውቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

62. ይህን በተመለከተ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ክፍያ የሚዘገየው በጥቃቅን ምክንያት አንድ ወይም ሁለት ቀን ሊዘገይ እንደሚችል በዚህ ምክንያት ተማሪዎቹ ወደ ሌላ ነገር ይሄዳሉ የሚባለው ነገር ተቀባይነት እንደሌለው ሆኖም ቀረ የኪስ ገንዘባቸው በየ30 ቀኑ አንዳንዴም ከዚህም ባነሰ ቀን ይደርሳቸዋል፡፡ ተጨማሪዋ 90 ብር ማለትም ከ330 ወደ 420 የተጨመረው ሰርኩላሩ ለዩንቨርስቲዎች ብቻ የተላለፈ በመሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን አሁን የአስተዳደር ዲኑ ጉዳዩን ይዞ ጫፍ ለማድረስ የተቃረበ ሲሆን እስከአሁን አለመደረጉ እንደ ክፍተት የሚቀበሉት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

63. በተጨማሪ በመውጫ ስብሰባ ወቅት የነበሩ ኃላፊዎች እንደገለፁት ክፍያው የሚዘገየው የተማሪዎች ስም ዝርዝር ከዲፖርትመንት ወደ ፋይናንስ ከፋይናንስ ተጨርሶ ለፊርማ ባለው የስራ ሂደት በየክፍሉ አንድ ሁለት ቀን በመዘግየቱ ምክንያት በመሆኑ ነው በማለት የገለፁ ሲሆን ስለተጨማሪው ብር 90 በተመለከተ ሰርኩላሩ ለዩኒቨርስቲዎች ብቻ የተላለፈ በመሆኑና ነገር ግን አሁን የአዲስ አበባ ንግድ ስራ ኮሌጅ የተፈቀደበትን ግልባጭ(ኮፒ) በመያዝ ከጥር 2006 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን ለመክፈል በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

64. በመሆኑም ለተማሪዎች ከመንግስት የሚሰጠው ገንዘብ በወቅቱ አለመከፈልም ሆነ የሚደረጉ ጭማሪዎች በጊዜያቸው የማይፈቀድና የማይሰጣቸው ከሆነ ተማሪዎች በአብዛኛው ከክልል የሚመጡና ከፍተኛ ወጪ ማለትም የቤት ኪራይ፣ ምግብ፣ ጤና፣ ፅዳትና የተለያዩ የትምህርት መረጃዎች ኮፒ ማድረጊያና መግዣ የመሳሰሉት ወጪ ያለባቸው በመሆኑ በመማር ማስተማሩ ሂደትን ሊያስተጓጉለው የሚችል መሆኑን ሊጤን ይገባል፡፡

## ለማዕከሉ አስተማሪዎች የስራ መዘርዝር የሚደርስ መሆኑን በተመለከተ

65. ማዕከሉ በስሩ ለሚገኙ ሠራተኞች የስራ መዘርዝር በማዘጋጀትና በመስጠት ስራቸውን በወቅቱ እንዲሰሩ ማድረግ ይገባዋል፡፡

66. በማዕከሉ በስሩ ለሚሰሩ ሰራተኞችም ሆነ ለተማሪዎች የሚሆን የስነ ምግባር መመሪያ ሊያዘጋጅና ሊተገብር ወይም የስራ መዘርዝር(Job discribtion) በማዘጋጀት ለሰራተኞች ሊያደርስ ይገባል፡፡

67. ሆኖም ማዕከሉ በስሩ ለሚገኙ አስተዳደር ሰራተኞች የስራ መዘርዝር እያዘጋጀ የሚሰጥ ቢሆንም ለአስተማሪዎች ወይም ለአካዳሚክ ክፍሎች ተዘጋጅቶ ያልተሰጣቸውና ለተማሪዎችም አዲስ ሲገቡ የመግቢያ ገለፃ (orientation) ብቻ የሚደረግላቸው ቢሆንም በፅሁፍ የማይደርሳቸው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተደረገ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. የሆቴልና ቱሪዝም ዲፖርትመንት ይህን በተመለከተ ተጠይቀው በማዕከሉ የተዘጋጀ Legistlation (መመሪያ) ቢኖርም ተግባራዊነቱ ላይ ክፍተት መኖሩን ለተማሪዎች ለሥልጠና ሲገቡ በሁለት ሣምንት ውስጥ ስለመመሪያው ገለፃ ይደረጋል ነገር ግን በእጃቸው አይሰጣቸውም በማለት ገልፀዋል፡፡

69. የቱሪዝም ዲፖርትመንትም ይህን በተመለከተ ተማሪዎች ለሥልጠና ሲገቡ በሁለት ሣምንት ውስጥ የመግቢያ ገለፃ ይደረግላቸዋል ነገር ግን በእጃቸው በፅሁፍ

አይሰጣቸውም ቢሰጥ ግን ጥሩ ነበር፡፡ ለመምህራን የሚደረግ ገለፃም ሆነ የሚሰጣቸው ነገር የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

70. አካዳሚክ ዲኑ ለአስተማሪዎች የስራ መዘርዝር ተዘጋጅቶ አለመድረሱን በተመለከተ ለአስተማሪዎች የስራ መዘርዝር አልደረሰም ይህን የመስጠት ግዴታ ያለበት የሰው ኃይል ክፍል ነው፡፡ ባለመሰጠቱ መምህራኖች ከማስተማር ውጪ ያለውን የስራ ድርሻቸውን አውቀው እንዳይሰሩ አድርጓቸዋል በማለት ገልፀዋል፡፡

71. በመቀጠል የሰው ኃይል ዳይሬክቶሬት ይህን በተመለከተ ሲገልፁ ለአስተማሪዎች የስራ መዘርዝር በማዘጋጀት ሊያደርሱ የሚገባው የዲፓርትመንት ኃላፊዎች ናቸው እንጂ የሰው ኃይሉ አይደለም፡፡ በሌሎች ዩኒቨርስቲዎችም የሚያዘጋጁት ዲፓርትመንት ክፍሎች ናቸው በማለት ገልፀዋል፡፡

72. በመሆኑም ማዕከሉ በሚመለከተው አካል ለአስተማሪዎች የስራ መዘርዝር በማዘጋጀት ሊያደርስ ባለመቻሉ አስተማሪዎች በትክክል መተግበር ያለባቸውን ስራ እንዳይወጡ የሚያደርግ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

## <u>በማዕከሉ ተማሪዎች የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት ሞዴል ሆቴል መኖሩን በተመለከተ</u>

73. ማዕከሉ ሞዴል ሆቴል በመገንባት ተማሪዎች የተግባር ልምምድ ሊያደርጉበትና ሊቆጣጠረው ይገባል፡፡

74. ማዕከሉ ከነሐሴ 08/1989 ዓ.ም ጀምሮ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ አማካይነት በራስ ሆቴሎች አስተዳደር ድርጅት ስር የነበረው የገነት ሆቴል ድርጅትን ለሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛነት እንዲውል የተወሰነ ሲሆን በዚሁ መሠረት ማዕከሉ በገነት ሆቴል ታችኛው ግቢ ባለ ሶስት(3) ኮከብ ሞዴል ሆቴል ለመገንባትና ለመቆጣጠር የታሰበ ቢሆንም የሞዴል ሆቴል ግንባታ ስራ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ ታውቋል፡፡

75. ይኸውም ማዕከሉ የገነት ሆቴል ድርጅትን ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ የተረከበና ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ ባክቴክ በተባለ አማካሪ መሐንዲስ ድርጅት የሞዴል ሆቴል ዲዛይን ለማዘጋጀት ከማዕከሉ ጋር ውል በመዋዋል ጥናት ተዘጋጅቶ የቀረበ እና እስከ 1993 ዓ.ም. በተጠናው የዲዛይን ጥናት መሰረት በወቅቱ በነበሩ አመራሮች የግንባታ ስራዎች ሳይሰሩ አራት ዓመት በማስቆጠሩ ከባክቴክ አማካሪ ጋር የነበረው ውል የተቋረጠ እና የሞዴል ሆቴል ስራው (ግንባታው) ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ ከማዕከሉ እና ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ከተፃፉ ደብዳቤዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

76. የማዕከሉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ስለ ሞዴል ሆቴሉ ግንባታ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ማዕከሉ የሚያውቀውና የተቋረጠው ፕሮጀክት ሞዴል ሆቴል ሳይሆን የሆቴሉን መኝታ ክፍሎች ወደ ስልጠና ማዕከልነት የመቀየር ፕሮጀክት ነው፡፡ የሞዴል ሆቴሉን ፕሮጀክት በ2008 ዓ.ም የዲዛይን ስራ ለማከናወን በዕቅድ ተይዟል በማለት ገልፀዋል፡፡

77. ሆኖም ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ይህንን ይበሉ እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከሰነድ መረጃ ለማወቅ እንደተቻለው ማዕከሉ የገነት ሆቴል ድርጅትን እንደተረከበ በባክቴክ አማካሪ መሐንዲስ የተጠናው የዲዛይን ጥናት የሞዴል ሆቴልን ፕሮጀክት ለመስራት ስለመሆኑ ከቀድሞ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮሚሽን/ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር/ ጋር ሆነ ከተለያዩ አካላት ጋር ከ1987-1994 ዓ.ም ከተፃፉ ደብዳቤዎችና ማዕከሉ ለቱሪዝም ኮሚሽን በላከው የውል ስምምነት ላይ ከባክቴክ አማካሪ ማሐንዲስ ጋር የተፈራረመው የውል ስምምነት ላይ የሞዴል ሆቴልና ፕሮጀክት ሥራ የሚል መሆኑን እንዲሁም በቁጥር 105/7.1/93 በቀን 15 ግንቦት 1993 ዓ.ም የተፃፈ ደብዳቤ ስለሞዴል ሆቴል ግንባታ የሚገልጽ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

78. በመሆኑም በማዕከሉ ሞዴል ሆቴል ግንባታ ባለመኖሩ ተማሪዎች የተግባር ልምምድ ለማድረግ የተለያዩ ሆቴሎች በመሄድ ልምምዱን እንዲያደርጉ ያደረገ መሆኑ ይህም የተግባር ስልጠናውን በሚገባ እንዳይከናወን ሊያደርገው የሚችል መሆኑ፣ ለተጨማሪ ጊዜና ወጪ የሚዳርጋቸው መሆኑና ማዕከሉም ሆነ መንግስት ከሞዴል ሆቴሉ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም እንዳያገኙ እያደረገ ይገኛል፡፡

### <u>በገነት ሆቴል የሚገኙ የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማስተማሪያ ክፍሎች ለመለወጥ የሚደረግ የዕድሳት ስራን በተመለከተ፣</u>

79. ሰልጣኞች በተመቻቸ ሁኔታ ስልጠና እንዲያገኙ በገነት ሆቴል የሚገኙ የመኝታ ክፍሎች ወደ ማስተማሪያ፣ ሰርቶማሳያና ወደቢሮነት ለመቀየር የተጀመረው የግንባታ ሂደት በማፋጠን ተማሪዎች በተመቻቸ ሁኔታ ስልጠና ሊያገኙ ይገባል፡፡

80. ይሁን እንጂ በ1998 ዓ.ም ጊዲዮን ደመቀ የተባለ አማካሪ መሐንዲስ በገነት ሆቴል የሚገኙ 104 የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማሰልጠኛና የተግባር መለማመጃ ክፍሎች ለመቀየር የዲዛይን ሥራን ጨረታ በማሸነፍ የዲዛይን ጥናት በማካሄድ ዲዛይን ሰርቶ ያቀረበ ሲሆን በዲዛይኑ ላይ በክለሳ ወቅት አስፈላጊ የሆነ የብረት አይነት በአግባቡ አለመጠቀሱን በሬንቦ አርክቴክቸር ተቆጣጣሪ መሐንዲስ በመገለፁና በዚሁ መሠረት ጌዲዮን ደመቀ ተቋራጭ አሟልቶ ማቅረብ ባለመቻሉ ለዚህም ብር 86,250

የተከፈለው መሆኑን ዲዛይኑም ተቀባይነት ሳያገኝ እንደቀረ ከማዕከሉ እና ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ከተፃፉ ደብዳቤዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

81. በመቀጠልም በ2000 ዓ.ም. የግንባታ ስራውን ለመቆጣጠር በጨረታ ያሸነፈው ሬይንቦ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ካሸነፈበት ዋጋ ከ25 በመቶ ባልበለጠ ዋጋ ስትራክቸራል ዲዛይኑን ያለጨረታ እንዲሰራ መደረጉ፣ ሬይንቦም የዲዛይን ጥናቱን በማዘጋጀት ያቀረበ ሲሆን ትክክለኛነቱ ሳይገመገም(ሳይጣራ) ለዚሁ ሥራ ብር 237,950 የተከፈለው መሆኑን ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

82. በተጨማሪም በ2001 ዓ.ም ሬንቦ አርክቴክቸር ለሁለተኛ ጊዜ ባዘጋጀው ዲዛይን መሰረት ሳሙኤል ሣህለማርያም ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ድርጅት የግንባታ ሥራውን ለመስራት የጨረታ ኮሚቴ ውሳኔ ቃለ ጉባኤ በስተቀር ሌሎች ጨረታውን የሚመለከቱ ማስረጃዎቸው እና ውል የተዋዋለበት ሰነድ ለኦዲት መቅረብ አለመቻሉና እንዲሁም ተቋራጩ የዕድሳት ሥራውን ከጀመረ እና ብር 4,177,119 ከተከፈለው በኃላ ዲዛይኑ ችግር ያለበት መሆኑን በመግለጹ ከሰኔ 22/2003 ዓ.ም.ጀምሮ ውሉ የተቋረጠ መሆኑን ከተቋራጩ ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከማዕከሉ ውሉ እንደተቋረጠ ከተጻፈ ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

83. እንዲሁም በ2002 ዓ.ም ለዚሁ የግንባታ ዕድሳት ስራ ለዲዛይን ሥራው በውስን ጨረታ የተቀጠረው አማካሪ ኤምኤች ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ ለሶስተኛ ጊዜ የዲዛይን ሥራውን እንዲያከናውን የተደረገ መሆኑን እና ለዚሁ የዲዛይን ሥራው የኮንትራት ውል ስምምነት ለኦዲት ቡዱኑ ማቅረብ አለመቻሉ፣ ለዚሁ የዲዛይን ስራ ብር 267,882 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን እና የተፈፀመው ክፍያ በውሉ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ አለመቻሉ በኦዲት ወቅት ከማዕከሉ ከተጻፉ ደብዳቤዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

84. በተጨማሪ በኤም ኤች ኢንጅነሪግ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ ለሶስተኛ ጊዜ ባቀረበው ዲዛይን መሰረት ለግንባታ ሥራው የተጠየቀው ዋጋ ከብር 10,318,719 ወደ 23,503,293 በ127.8% ከፍ በማለቱ እና ተጨማሪ ወጪ የሚጠይቅ ሆኖ በመገኘቱ ከሳሙኤል ሣህለ ማርያም የስራ ተቋራጭ ጋር የነበረው ውል ሰኔ 22/2003 ዓ.ም. ጀምሮ የተቋረጠ መሆኑን ከማዕከሉ ከተፃፈ ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

85. በአጠቃላይ የኦዲት ቡድኑ ተጀምሮ የተቋረጠውን የግንባታ ስራውን በመስክ በተመለከተበት ወቅት በሮችና መስኮቶች የሌሉት፣ ኮርኒሶች የተነቃቀሉ፣ የመታጠቢያ ቤት ዕቃዎች በሜዳ ላይ የተጣሉ መሆናቸው፣ በግቢው ውስጥ እና በግንባታው ቦታ ሳርና የተለያዩ እፅዋት በቅለውበት መታየታቸው በአጠቃላይ ለዕድሳት ስራው ከተለያዩ ወጪዎች ጋር ከ4 ሚሊዮን ብር በላይ የወጣበት መሆኑን እና ውጤታማ አለመሆኑን በተደረገ የመስክ ምልከታና ከክፍያ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡





ፎቶ 2 በገነት ሆቴል የዕድሳት ስራ ተጀምረው የተቋረጡ እና የፈራረሱ የመኝታ ክፍሎች



ፎቶ 3 በገነት ሆቴል ተጀምሮ የነበረው የዕድሳት ስራ የተለያየ እጽዋቶች በቅለውበት እና ዕቃዎች ሜዳላይ ወድቀው



ፎቶ 4 በገነት ሆቴል ተጀምሮ የነበረው የዕድሳት ስራ ጣራው ተነቃቅሎ የሚያሳይ

86. የዕድሳት ስራውን በተመለከተ ሳሙኤል ሳህለማርያም የስራ ተቋራጭን ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ጨረታውን አሸንፌው ስራ ከጀመሩ እና ሰላሳ በመቶ (30%) ያክል ካከናወኑ በኋላ የነበረው ህንጻ ከተገነባ ብዙ ዓመት የቆየ በመሆኑ በዚያው ላይ ቢቀጥል ለረዥም ጊዜ የማያገለግል መሆኑን በመገንዘባቸው ዲዛይኑ መቀየር እና መስተካከል ያለበት መሆኑን ጥያቄ ማቅረባቸውን ገልጸዋል፡፡ በዚሁ መሰረትም የተጠናው ጥናት በሚመለከተው አካል ታይቶ ዲዛይኑ መለወጥ እንዳለበት ተወስኖ ዲዛይኑን ያዘጋጀው አማካሪ መሃንዲስ ሬንቦ ዲዛይኑን ለመከለስ ፈቃደኛ ባለመሆኑ በሌላ አማካሪ መሃንዲስ ኤም ኤች በተባለ ዲዛይኑን እንዲያዘጋጅ ተደርጎ በተሰራው ዲዛይን መሠረት የግንባታ ዋጋው ብር 23 ሚሊዮን የሚጠይቅ ሆኖ በመገኘቱ ጭማሪው (127%) በመሆኑ በግዢ መመሪያ መሠረት ሌላ የስራ ተቋራጭ እንደገና መመረጥ ያለበት ሆኖ በመገኘቱ ከሳሙኤል ጋር የነበረው ውል በሰኔ 2003 ዓ.ም. የተቋረጠ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

87. የግንባታ መጓተትን እና ዲዛይን በየጊዜው መቀያየሩን በተመለከተ የማዕከሉ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በወቅቱ እንዳልነበሩና ስለጉዳዩ የማያውቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በ2006 ዓ.ም ከባህልና ቱሪዝም የዕድሳት ስራውን እንዲቆጣጠር ለማዕከሉ ኃላፊነት የተሰጠውና ስራውን ለመጀመር ከኤም ኤች ኢንጂነሪንግ ጋር ውል የተፈራረሙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡



ፎቶ 5 በዕድሳት ላይ የሚገኘው የመማሪያ ክፍል ኮርኒሱ ተገነጣጥሎ የሚያሳይ

88. ሆኖም እኛ እንደተገነዘብነው 104 የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማስተማሪያነት ክፍል የመቀየር የግንባታ ሂደት ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ ተፈቅዶ ላለፉት 16 ዓመታት ግንባታው ሳይጠናቀቅ መቅረቱ ለዚሁ የግንባታ ሥራ የዲዛይን ሥራውን ለማከናወን በተለያየ ጊዜ ሶስት/3/ አማካሪ መሃንዲሶች መቀያየራቸው የዲዛይኑ ሥራ ለሶስተኛ ጊዜ መቀየሩ በዚሁ መሠረት ለእያንዳንዱ አማካሪ ላቀረበው ዲዛይን ሥራ በትክክል ለመሰራቱ ሳይጣራ ክፍያ መፈጸሙ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም ለሳህለማርያም ሥራ ተቋራጭ የግንባታ ሥራው ከመጀመሩ በፊት ዲዛይኑ በትክክል መጣራት ሲገባው ሳይጣራ ስራ እንዲጀምር መደረጉና ለሥራ ተቋራጩ ብር 4,177,119 ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ዲዛይኑ ችግር አለበት በማለት ሥራ እንዳይቀጥል መደረጉ ገንዘቡን ለብክነት የዳረገው እና ምንም ውጤት እንዳልተገኘበት ያሳያል፡፡

89. ግንባታው ለ16 ዓመታት ያህል ሳይከናወን መቅረቱ ተማሪዎች ተገቢውን ስልጠና እንዳያገኙ፣ በቦታ እጥረት እና በቢሮ ጥበት አሰልጣኞች እና ሰልጣኞች በተመቻቸ ሁኔታ ስልጠናውን እንዳይሰጡ እና እንዳይከናወን አድርጓል፡፡ የገነት ሆቴል የመኝታ ክፍሎች በ2001 ዓ.ም በመፍረሳቸው ምክንያት ለ6 ዓመታት ሆቴሉ ከመኝታ

አገልግሎት ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ ያሳጣውና መንግስትም ማግኘት የነበረበትን ገቢ እንዳያገኝ ያደረገው መሆኑም ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

## የማዕከሉ የትምህርት መስጫ ክፍሎችን በተመለከተ

90. የማዕከሉ የቱሪዝም እና የሆቴል የትምህርት ዘርፍ ማሰልጠኛ ክፍሎች ከተማሪዎች ቁጥር አንጻር በቂ እና የተሟላ እንዲሁም ለመማር ማስተማር ሂደቱ አመቺ ሊሆን ይገባል፡፡

91. ይሁን እንጂ ተማሪዎች ስልጠና የሚወስዱበት በገነት ሆቴል በሚገኙ ለጊዜው በተሰሩ ስምንት (8) የማሰልጠኛ ክፍሎች ሲሆን ክፍሎችም ጠባብና ከቆርቆሮ የተሰሩ መሆኑ፣ የአየር ሁኔታው ሙቀት ሲሆን በጣም የሚሞቁ፣ አየሩ ቀዝቃዛ ሲሆንም በጣም የሚቀዘቅዙ በመሆናቸው፣ ስልጠናው ምቹ ባልሆነ ሁኔታ እየተካሄደ የሚገኝ በመሆኑ ተማሪዎችም ሆኑ አስተማሪዎች በሙቀት ስለሚጨናነቁ የመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ትኩረት እንዳይሰጡ ያደረገ መሆኑን በናሙና ተመርጠው መጠይቅ ከተደረገላቸው ተማሪዎችና በመስክ ጉብኝት ወቅት በተደረገ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡





ፎቶ 6 በገነት ሆቴል ተማሪዎች እየተማሩ የሚገኙባቸው በጊዜያዊነት በቆርቆሮ የተሰሩ ክፍሎች

92. ስለሁኔታው የቱሪዝም ዲፓርትመንትም ኃላፊ ተጠይቀው ሲመልሱ የቱሪዝም ሥልጠና በባህሪው ዘመናዊ መሆኑን ሆኖም የመማሪያ ክፍሎቹ ዘመናዊ አለመሆናቸውን በቆርቆሮ የተሰሩ የመማሪያ ክፍሎች ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች የተመቻቹ አለመሆናቸው፣ የቆርቆሮ የስልጠና ክፍሎች ሲዘጋጁ ለ6 ወር ብቻ ተብሎ የተዘጋጁ ቢሆንም (ከሁለት ዓመት በላይ) ተማሪዎች በዚህ ክፍል ስልጠና እየተሰጠ

መገኘቱን ለዚህም ምክንያቱ  የገነት ሆቴል የግንባታ ስራው መጓተቱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

93. እንዲሁም የሆቴል ዲፓርትመንት ኃላፊ ተጠይቀው የሰጡት መልስ የገነት ሆቴል ዕድሳት ስራ መጓተት ተገቢውን ስልጠና ተማሪዎች አግኝተው እንዳይወጡ ማድረጉን፣ በቦታ እጥረትና በቢሮ ጥበት አሰልጣኞች፣ ሰልጣኞች እና ሰራተኞች በተመቻቸ ሁኔታ ላይ አለመሆናቸውን፣ ተጨማሪ ስልጠና እንዳይሰጥ እና ለሌሎች መደገፍ የሚገባቸው አካላትን መደገፍ እንዳይቻል ያደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

94. ለተማሪውም፣ ለመምህራኑም ሆነ ለትምህርቱ በማይመቹና በማይመጥኑ ክፍሎች ውስጥ ስልጠና እየተሰጠ የትምህርት ጥራቱን በተሳካ ሁኔታ እንዴት ማስጠበቅ እንደሚቻል ግልፅ ካለመሆኑ ባሻገር በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ብቁና የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት አስቸጋሪ የሚያደርገው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

## <u>በገነት ሆቴል አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ 104 የመኝታ ክፍሎች በዕድሳት ወቅት የንብረት ርክክብን  በተመለከተ</u>

95. በገነት ሆቴል አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ 104 የመኝታ ክፍሎች ወደ ማስተማሪያና ሰርቶ ማሳያነት ለመቀየር የዕድሳት ስራ በሚሰራበት ወቅት በተገቢው መንገድ ርክክብ ሊደረግባቸውና በህግ እና ደንብ ተከትለው አገልግሎት እንዲሰጡ ወይም እንዲወገዱ ማድረግ ይገባል፡፡

96. ይሁን እንጂ በፊት የነበሩት 104 የመኝታ ክፍሎች በፈረሱበት ወቅት የክፍሎቹ በሮች እና መስኮቶች እንዲሁም ሌሎች ያገለገሉ ዕቃዎችን የእድሳት ስራውን ሲሰራ ከነበረው የሥራ ተቋራጭ ሳሙኤል ሳህለማርያም ጋር ሆቴሉ ርክክብ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተደረገ የመስክ ጉብኝት እና ከገነት ሆቴል ስራ አስኪያጅ ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

97. ይህን በተመለከተ ምክትል ዳይሬክተሩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በርና መስኮቶች ርክክብ የተደረጉት ለገነት ሆቴል መሆኑን ለማዕከሉ ርክክብ አለመደረጉን  ገልፀዋል፡፡

98. በተጨማሪ የገነት ሆቴል ስራ አስኪያጅ ስለሁኔታው ተጠይቀው ከተቋራጩ ጋር የተለያዩ ንብረቶች ርክክብ አለመደረጉን ገልጸው ነገር ግን እነዚህን ንብረቶች በተለያየ ጊዜ በጨረታ በማወዳደር  የተሸጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

99. በመሆኑም አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ የመኝታ ክፍሎችን ወደ ሰርቶ ማሳያነት ለመቀየር የዕድሳት ስራው ከመጀመሩ በፊት ሲያገለግሉ የነበሩ በሮችና መስኮቶች እንዲሁም ሌሎች ያገለገሉ እቃዎች ከተቋራጩ ጋር በተገቢው መንገድ ርክክብ ሊደረግባቸው ሲገባ አለመደረጋቸው ንብረቶቹ በትክክል ስለመወገዳቸው

የማያመላክት መሆኑን እና የመንግስት ንብረት ያለአግባብ ሊባክን እንደሚችል ሊታወቅ ይገባል፡፡

**<u>በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት እና ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት የተዘረጋ ስለመሆኑ፣</u>**

100. ማዕከሉ በሚሰጠው የስልጠና አገልግሎት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመለየትና ለችግሮቹም መፍትሄ ለማግኘት ይረዳ ዘንድ ከክልሎችም ሆነ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

101. ሆኖም ማዕከሉ በሆቴልና ቱሪዝም የሚታዩ ችግሮች ላይ ለመነጋገር በሸራተን አዲስ ከተለያዩ ዩኒቨርስቲ ከተውጣጡ አካላት ጋር የውይይት መድረክ በተዘጋጀበት ወቅት የተነሱ ችግሮች እና ጠቃሚ ተሞክሮዎችን በመለየት በህትመት መልክ ያላዘጋጀ እና ለባለድርሻ አካላት ያላሰራጨ መሆኑ፣ ለአስጎብኚ እና ለሆቴል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተለያዩ ስልጠናዎች ከተሰጡ በኋላ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት የተሻሻለ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት የሚሰራበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን ከ2004 ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡

102. ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ግንኙነትን በተመለከተ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለን ግንኙነት በሚፈለግ ደረጃ ላይ ያልደረሰ ቢሆንም በ2004 ዓ.ም እና በ2005 ዓ.ም መጨረሻ በጋራ በመስራት ጋር ተያይዞ ልዩ ልዩ ጭብጦች በማንሳት ተወያይተናል፡፡ በ2006 ዓ.ም ይህንን ተሞክሮ ከማስፋት ጋር ተያይዞ ባለድርሻ አካላት እንደ የአደረጃጀቶቻቸው በመለየት የጋራ ስምምነት ሰነድ ተፈራርመው አብረው በመስራት ላይ መሆናቸውንና በቀጣይም በበለጠ የሚያስፋፉት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

103. እንዲሁም የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ስልጠና ከወሰዱ በኋላ የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻላቸውን ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ብቃት ማረጋገጥ ጋር አብሮ አለመስራትን በተመለከተ ሲገልጹ ጉዳዩ ለማዕከሉ በደንብ (በህግ) ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ውጭ መሆኑን ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት ስልጠናዎች በመስጠት እንጂ የአገልግሎት ተቋማት ጥራት የመቆጣጠር ተግባር ለመፈፀም የሚያስችል ስርዓት የሌለ መሆኑን፣ በቅንጅት የሚሰሩትም እንደአስፈላጊነቱ ስልጠና በመስጠት መሆኑን የቁጥጥር ተግባር ግን የማዕከሉ አለመሆኑን የባህልና ቱሪዝም ሃላፊነት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

104. ሆኖም ማዕከሉ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት ወጥ የሆነ ስርዓት ባለመኖሩ በማዕከሉ የሚነሱ ችግሮች ጎልተው እንዳይወጡና ከባለድርሻ አካላት ጋር በሚደረግ ውይይት ሊገኝ የሚችሉ ችግር ፈቺ መፍትሄዎች እንዳይገኙ የሚያደርግ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡እንዲሁም ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብቃት ማረጋገጥ ጋር ያለው የስራ ትስስር ጠንካራ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የተቀመጠውን ግብ ውስን አፈፃፀም እንዲኖረው ያደረገ መሆኑን ሊታወቅ ይገባል፡፡

**<u>የማዕከሉ የመረጃ አያያዝ የተጠናከረ መሆኑን በተመለከተ</u>**

105. በማዕከሉ የሚሰለጥኑ ተማሪዎችን እና አስተማሪዎችን ሁኔታ የሚገልጽ መረጃ፣ በገነት ሆቴል ለሚሰራው የዕድሳት ስራ ላይ የተመረጡ የተሳተፉ አማካሪ መሀንዲሶችን እና ተቋራጮችን የሥራ ክንውን የሚገልጹ መረጃዎችን የመሳሰሉት በማዕከሉ በተደራጀ ሁኔታ እና ስርዓት ባለው መልኩ ሊያዙ ይገባል፡፡

106. ሆኖም በማዕከሉ አዲስ ተማሪዎች ምዝገባን በተመለከተ ቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም (TVET) በየዓመቱ የሚላኩ የመግቢያ መስፈርት፣ አዲስ የሚገቡ ተማሪዎች ከ2003-2005 ዓ.ም የተመረጡበት የምልመላ መስፈርት(ውጤት)፣ በማዕከሉ የተዘጋጀ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ/ከ2003-2005/፣ የ2003 በጀት ዓመት እና የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ፣ የባክቴክ አማካሪ መሃንዲስ ለአገልግሎቱ ክፍያ የተፈጸመበት መረጃ፣ የኤም. ኤች. አማካሪ መሃንዲስ ለዲዛይን ጥናት የተፈራረመው የውል ስምምነት ማስረጃ፣ የተቋራጭ ሳሙኤል ሳህለማርያም ለግንባታ ሥራው ከማዕከሉ ጋር የተፈራረመው የውል ማስረጃ እና የተሟላ ጨረታ መረጃዎች፣ የመሳሰሉት መረጃዎች በማዕከሉ ስርዓት ባለው መልኩ ያልተያዙ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት መረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ ባለመቅረቡ ምክንያት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

107. ይህን በተመለከተ የቱሪስት ዲፖርትመንት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ችግር ያለ መሆኑን ሆኖም በዲፓርትመንቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች እንደሚያዙ ነገር ግን የመረጃ አያያዝ ችግር በቦታ ጥበት ምክንያት የተከሰተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

108. የሆቴል ዲፓርትመንት ኃላፊም ስለሁኔታው ሲገልፁ በማዕከሉ የተጠናከረ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡

109. ምክትል ዋና ዳይሬክተሩም ይህን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የመረጃ አያያዝ ችግር በሁሉም የስራ ክፍሎችና ባለሙያዎች እኩል ደረጃ ባይኖረውም ችግሩ የሚታይባቸው የስራ ክፍሎችና ባለሙያዎች ለመረጃ ስርዓቱ ትኩረት አለመስጠት፣

የሥራ ዶክመቶችን  በአግባቡ ለማስቀመጥ ተነሳሽነት አለመኖር እና የቦታ ጥበት ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

110. ሆኖም ተማሪዎች በአብዛኛው ከክልል የሚመጡ በመሆናቸውና አስቀድመው ከመምጣታቸው በፊት ስለማዕከሉም ሆነ ስለስልጠናው መገንዘብ/ማወቅ/ የሚኖርባቸውን ነገሮች ለማወቅ መረጃ ክፍሉ ውስጥ የመገናኛ መስመር ስልክ እና ሙሉ መረጃ ሊኖር የሚገባ ሲሆን ባለመኖሩ ተማሪዎች ለእንግልትና ለተጨማሪ ወጪ እየዳረጋቸው የሚገኝ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በተጨማሪ ማዕከሉ ስለሚያስገነባው የገነት ሆቴል የመኝታ ክፍሎችን በተመለከተ የሚሳተፍ አማካሪም ሆነ ተጫራቾች የሚገልጽ መረጃ በተጠናከረ መልኩ ካልተያዙ ክትትል ለማድረግም ሆነ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘትና ውሳኔ ለማቅረብ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

111. የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ማዕከል በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ብቁና የሰለጠነ የሰው ኃይል ለኢንዱስትሪው በማቅረብ የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ የማሳደግ ስራ እንደሚሰራ ይታወቃል፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ማዕከል የተለያዩ ስልጠናዎች ለመስጠት የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን ማረጋገጥ እና በገነት ሆቴል ሊገነባ የታሰበው ሞዴል ሆቴል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እየተከናወነ መሆኑን ማጣራት ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ አንፃር በኦዲቱ ወቅት የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡፡

- በማዕከሉ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣ የ2003 በጀት ዓመት እና የ2004 በጀት ዓመት ዓመታዊ እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ፣ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች በንጽጽር መልክ የማይቀርብ መሆኑ፣
- በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚሰጡ ስልጠናዎች በተጠናከረ መልኩ ለመስጠት የሚያስፈልጉ የቅርብ ጊዜ እና በአስተማሪዎች እየተዘጋጁ የሚባዙ ሞጅሎች ከተማሪ ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ ያልሆኑና ተማሪዎች ተውሰው የሚጠቀሙበት መንገድ ያልተመቻቸ መሆኑ፣
- በቤተ መጽሐፍት ለተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች እና ለሌሎች ተገልጋዬች አገልግሎት ሊውል የሚችል የኢንተርኔት መስመር ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- ተማሪዎች የተግባር ልምምድ በሚያደርጉባቸው ክፍሎች ውስጥ የሚያገለግሉ የተግባር መለማመጃ መሳሪያዎች /ማቴሪያሎች/ የምግብ ዝግጅት የተግባር ክፍል ውስጥ ካሉ ማሽኖች ሰባቱ (7) የተበላሹ ና የማይሰሩ መሆኑ፣
- በማዕከሉ በ2005 ዓ.ም. ዓመታዊ እቅድ ላይ የሆቴል እና ቱሪዝምን በተመለከተ አስር(10) የጥናትና ምርምር ስራዎች በማጥናትና በማሳተም ለሚመለከተው አካል (ባለድርሻ) ለማሰራጨት የታቀደ ቢሆንም ያልተሰራጩ መሆኑ፣
- ከማዕከሉ ውጭ ባለው በገነት ሆቴል የሚሰጡ ስልጠናዎች ላይ የክፍለ ጊዜ ብክነት እንዳይኖርና ችግሩም ከተከሰተ ተማሪዎች የሚያሳውቁበት የሚካሱበት ሁኔታ ለማመቻቸትም ሆነ ለመቆጣጠር በማዕከሉ የተዘረጋ ስርዓት የሌለ መሆኑ፣

- በማዕከሉ ለሆቴል እና ቱሪዝም ዘርፍ አስተማሪዎች የስራ መዘርዝር ያልዘጋጀ መሆኑ፣
- ለሌሎች የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለተማሪዎች የሚሰጠው የኪስ ገንዘብ የተጨመረ ቢሆንም በማዕከሉ ለሚማሩ ተማሪዎች ተግባራዊ አለመደረጉ ፡፡
- በማዕከሉ ተማሪዎች የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት ሞዴል ሆቴል የሌለው መሆኑ፣
- በገነት ሆቴል የነበሩ 104 የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማስተማሪያነት የመቀየር ስራ ከ1998 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያየ ጊዜ ሶስት በተለያዩ አማካሪ መሃንዲሶች (ጌዲዮን ደመቀ፣ ሬይንቦ አርክቴክት፣ ኤምኤች ኢንጂነሪንግ) የዲዛይን ሥራው የተከናወነለት መሆኑ፣ ስራውን ለመስራት የተመረጡ አማካሪ ድርጅቶች የሚያቀርቡት ዲዛይን ትክክለኛነቱ ሳይጣራ ስራዎች እየተጀመሩ የሚቋረጥ መሆኑ፣
- በ1999 ዓ.ም. በሬንቦ አርክቴክቸር በተዘጋጀው ዲዛይን መሰረት የግንባታ ሥራው በሳሙኤል ሳህለ ማርያም ተጀምሮ ለተቋራጩ ብር 4,177,119 ከተከፈለው በኃላ በዲዛይን ምክንያት ግንባታው የተቋረጠ መሆኑ፣
- በገነት ሆቴል ሲያገለግሉ የነበሩ (104) የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማስተማሪያነት ለመቀየር የተጀመረው የዕድሳት ስራ በሚከናወንበት ወቅት በፊት የነበሩ በሮችና መስኮቶችን በተቋራጭ እና በሆቴሉ አስተዳደር መካከል ርክክብ ሳይደረግ የተወገዱ መሆኑ፣
- ተማሪዎች በአሁኑ ጊዜ ስልጠና የሚሰጣቸው በገነት ሆቴል በቆርቆሮ በተሰሩ ክፍሎች መሆኑ፣
- ለገነት ሆቴል የሚገኙ የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማስተማሪያነት ለመቀየር የወጣው ከ4 ሚሊዮን ብር በላይ መሆኑና ምንም ዓይነት ጥቅም ያላስገኘና ስራው የተቋረጠ መሆኑ፣
- በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመለየትና ለመፍታት ወጥ የሆነ የመወያያ መድረክ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- በማዕከሉ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ያልተዘረጋና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣

ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች ካልተወገዱ ወይም ካልተቃለሉ በማዕከሉ የሚሰጠው የትምህርት አሰጣጥ ላይና ትምህርቱን የሚወስዱ ተማሪዎች ማግኘት የሚገባቸውን ዕውቀት እንዳያገኙ የሚዳርግ በመሆኑ በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች

እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

4.1 ማሰልጠኛ ማዕከሉ የሚሰጣቸውን ስልጠናዎች እንዲሁም በስሩ የሚያከናውነውን የሞዴል ሆቴል እና የማሰልጠኛ ክፍሎች የዕድሳት ስራን በብቃት፣ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት እና ለማከናወን የሚያስችሉ የሚከተሉት የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

- ማዕከሉ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያዘጋጅና በስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት በየበጀት ዓመቱ ያልተጋነነ ዕቅድ ሊያዘጋጅና በዕቅዱ መሠረት ሊተገብር ይገባል፡፡

- በማዕከሉ አዲስ እየተዘጋጁና እየተባዙ በቤተ መጽሐፍ (ላይብረሪ) ባልተቀመጡ የሞጅል ዓይነቶች ላይም በተጠናከረ ሁኔታ ሊቀጥል እና በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ለስልጠና የሚያገለግሉና በገበያ ላይ ብዙም የማይገኙ መጻህፍቶች ማዕከሉ በኮፒ በማባዛትና በላይብረሪ በማስቀመጥ ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች በመጻህፍቱ ሊገለገሉ የሚችሉ አካላት ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

- በማዕከሉ የሚሰጠው የስልጠና ሂደት 30% በንድፈ ሃሳብ እና 70% በተግባር በመሆኑና በአብዛኛውን ተማሪዎች ዕውቀት የሚሸምቱት በተግባር ልምምድ ወቅት በመሆኑ የተግባር ልምምድ በሚያደርጉበት ክፍል የሚገኙና የተበላሹ ዕቃዎች በማሰራትም ሆነ አዲስ በመግዛት የግብዓት ችግር ሊወገድና ሊሟሉ ይገባል፡፡

- በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ያሉ ችግሮችን በመለየት ለዘርፉ መሻሻል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማጥናት እና በማዘጋጀት ለባለድርሻ አካላት ሊያደርስ ይገባል፡፡

- በስልጠና አሰጣጥ ላይ የሚከሰቱ የክፍለ ጊዜ ብክነትን ለመቆጣጠርም ሆነ ተማሪዎች ለተግባር ልምምድ ወደ ተለያዩ ሆቴሎችና የቱሪስት መዳረሻ

በሚሄዱበት ወቅት ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ለማዕከሉ በመንግስት የሚሰጠው የተማሪዎች የኪስ ገንዘብ በወቅቱ ሊደርስና ለሌሎች የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተደረገው ጭማሪ /ብር90/ ማዕከሉ መንግስትን በማስፈቀድ ለማዕከሉ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ማዕከሉ ለተግባር መለማመጃ አገልግሎት የሚሆን ሞዴል ሆቴልን በመገንባት ሊቆጣጠርና ተማሪዎች የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

- በገነት ሆቴል የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማስተማሪያነት ለመለወጥ የተጀመረው የዕድሳት ስራ በመቀጠልና በፍጥነት እንዲጠናቀቅ በማድረግ ማዕከሉ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራና ተማሪዎችም ሆኑ አስተማሪዎች በተመቻቸ ሁኔታ የስልጠና አሰጣጥ ሂደት የሚካሄድበት ሁኔታ ሊያፋጥን ይገባል፡፡

- በገነት ሆቴል ሲያገለግሉ የነበሩ የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማስተማሪያ ክፍልነት ለመቀየር የተጀመረው የዕድሳት ስራ ወቅት ከፈረሱ ክፍሎች የተወገዱ ንብረቶች (ዕቃዎች) ርክክብ ሊደረግባቸውና በተገቢው መንገድ ሊወገዱ ይገባል፡፡

- በማዕከሉ የሚደረጉ ማንኛውም ለግንባታና የዕድሳት ስራ ወጪ የሚደረጉ ሂሳቦችን/ገንዘብ/ ማዕከሉ ሊቆጣጠርና የሚወጣው ወጪ ጥቅም ማስገኘቱን መገምገምና መቆጣጠር አለበት፡፡

- ማዕከሉ ከባለድርሻ አካላት ጋር በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመለየት፣ ለመፍታት እንዲሁም የልምድ ተሞክሮ ለመለዋወጥ የሚያመችና ወጥ የሆነ የመወያያ መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

- በማዕከሉ አዲስ የሚገቡ ተማሪዎች ተመልምለው የመጡበትን ሁኔታ የሚገልጽ ማስረጃ በእያንዳንዱ ተማሪ ማህደር ሊኖር፣ የተለያዩ ከቴክኒክ እና

ሙ.ያ(TEVT) የሚላኩ መስፈርቶች፣ በግንባታ ስራ የሚሳተፉ አማካሪዎችና ተቋራጮች የሚመለከቱ የጨረታ ዶክመንቶች /መረጃዎች/ እንዲሁም የውል ስምምነቶች የመሳሰሉት መረጃዎች በማዕከሉ የስልጠና አሰጣጡን የሚያፋጥኑ መረጃዎች ሊኖሩ እና መረጃውን ሊኖሩና በተደራጀ እና ስርዓት ባለው መልኩ ሊቀመጡ ይገባል፡፡

በመጨረሻም ለማዕከሉ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች፣ ለገነት ሆቴል ስራ አስኪያጅ፣ በማዕከሉ ለሚማሩ ተማሪዎች እንዲሁም ለሥራ ተቋራጮች በኦዲቱ ወቅት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

**አባሪ 1**

# የመመዘኛመስፈርቶች
# /EVALUATIVE CRITERIA/

| ተ.ቁ | የኦዲትጭብጥ / ISSUES/ Sub issues/ | የመመዘኛመስፈርቶች /EVALUATIVE CRITERIA/ |
|---|---|---|
| 1 | ማሰልጠኛ ማዕከሉ የሚሰጣቸውን ስልጠናዎች በብቃት ለማከናወን የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን ማረጋገጥ፣ | |
| | | 1. ማዕከሉ ለስልጠና አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ የተለያዩ መመሪያዎችን በማውጣት በተግባር ላይ ሊያውል ይገባል፡፡ |
| | | 2. ማዕከሉ የሚሰጠውን የስልጠና ጥራት በበቂ ሁኔታ ለመስጠት የሚያስችሉና ከወቅቱ ስርዓተ ትምህርት ጋር የሚዛመዱ የስልጠና ማቴሪያሎች ሊዘጋጁና ለተማሪዎች ሊደርሱ ይገባል፡፡ |
| | | 3. አዲስ በማዕከሉ ለሚሰለጥኑ ሰልጣኞች የመምረጫ መስፈርት ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | | 4. በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ለሚሰለጥኑ ሰልጣኞች ውጤት አሰጣጥ ትምህርት ሚኒስቴር በሚያወጣው ደንብ መሰረት መሆን አለበት፡፡ |
| | | 5. ከተለያዩ የውስጥ ገቢ የሚገኝ ምንጭ አጠቃቀም የመንግስትን ደንብና ህግ በተከተለ መልኩ መሆን ይገባል፡፡ |
| | | 6. በማዕከሉ የሚሰለጥኑ ተማሪዎች ስልጠና ከወሰዱ በኋላ የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት ሞዴል ሆቴል ሊኖረው እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | | 7. በማዕከሉ ስልጠና የሚወስዱ ተማሪዎች ቁጥር በየዓመቱ ሊጨምር ይገባል፡፡ |
| | | 8. ማዕከሉ በየዓመቱ ዕቅድ በማቀድ ስራዎችን ሊያከናውን ይገባል፡፡ |
| | | 9. የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች አፃፃፍ ግልፅነትና ወጥነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| | | 10.ማእከሉ በስሩ ለሚሰሩ መምህራን የአቅም ግንባታ በመስጠት ጥራት ያለው የትምህርት ስልጠና የሚሰጥበትን ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 11. ማእከሉ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚታዩ ጥቅሞችን የሚያሳይ እንዲሁም በዘርፉ የሚታዩ ችግር ፈች የሆኑ የተለያዩ ጥናትና ምርምር ሊያከናውን ይገባል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | | 12.ማእከሉ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ያከናወናቸውን የጥናትና ምርምር ውጤቶች በወቅቱ ለህትመት በማብቃት ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | | 13.ማእከሉ የሚሰጣቸውን የስልጠና ዓይነቶች ሊያሳድግ እና ደረጃቸውንም ከፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 14.ማሰልጠኛ ማእከሉ የተለያዩ ዘመናዊ የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የመማሪያ መጽሃፍትን አሟልቶ ተግባር ተኮር ስልጠና መስጠት የሚያስችል አደረጃጀት ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | | 15.የማእከሉ ተማሪዎች ለልምምድ ተግባር ወደ ተለያዩ ሆቴሎችና የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሲሄዱ በተግባር ልምምዳቸው ወቅት ከማእከሉ አስፈላጊው ክትትልና ቅጥጥር ሊደረግባቸው የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 16.በስልጠና ሂደቱ ላይ የክፍለ ጊዜ ብክነት እንዳይኖር ሰልጣኞችን ያሳተፈ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋ ይጋባል፡፡ |
| | | 17.የቱሪስት መዳረሻ አካባቢ ለተቋቋሙና ለሚቋቋሙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ልዩ ትኩረት በመስጠት ሙያዊ የምክር አገልግሎትና አጫጭር ስልጠናዎች የሚሰጡበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ |
| | | 18.ማሰልጠኛ ማእከሉ መምህራንና ተማሪዎች የሚገዙበት እና የሚተዳደሩበት የስነ ምግባር መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 2 | በማዕከሉ ሊገነባ የታሰበው የሞዴል ሆቴል ስራ መተግበሩን ማጣራትና መገምገም፤ | 19.ሊሰራ የታሰበው ሞዴል ሆቴል በእቅዱ መሰረት ስራው ሊፋጠንና ስራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡ |
| | | 20.የሞዴል ሆቴል ግንባታው ላይ የሚሳተፈው የተቋራጭ ድርጅት ዓመራረጥ በመንግስት የአገልግሎት ግዥ መሰረት መሆን አለበት፡፡ |
| | | 21.ለገነት ሆቴል ግንባታና እድሳት ስራ የሚከፈለው ገንዘብ በአግባቡ ኢኮነሚያዊ ተቀሜታ በሚሰጥ መልኩ ተግባር ላይ ሊውል ይገባል፡፡ |
| 3 | ማዕከሉ፤ከክልሎች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርዓት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፤ | 22.ማእከሉ በገነት ሆቴል ድርጅት የስራ አፈጻጸም ላይ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 23. ማእከሉ የቱሪዝም መዳረሻ የሆኑ ቦታዎችን በመለየት እና የማሰልጠኛ ተቋም በመክፈት አድማሱን ሊያሰፋ ይገባል፡፡ |
| | | 24. ማእከሉ የአስጎብኚ እና የሆቴል አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራታቸውን እንዲያሻሽሉ የተለያዩ ስልጠናዎች ከሰጠ በኋላ ጥራታቸውን ማሻሻላቸው ለማረጋገጥ እንዲያስችለው ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብቃት ማረጋገጥ ክፍል ጋር አብሮ በቅንጅት ሊሰራ የሚያስችለውን ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 25.ማዕከሉ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት |

| | | |
|---|---|---|
| | | የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 26.በማዕከሉ የተጠናከረ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | | 27.ከባለድርሻ አካላት ጋር ወጥ የሆነ የመወያያ መድረክ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | | 28.በሆቴልና ቱሪዝም መስክ በዓበይትና ወቅታዊ ጉዳዮች፣ በምርምር ውጤቶችና አዳዲስ አስተሳሰቦች ላይ ሴሚናሮች፣ ሲምፖዚየሞችንና ወርክሾፖችን ከሚመለከታቸው አከላት ጋር በመተባበር ማዕከሉ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | | 29.በሃገር ውስጥና በሌሎች ሃገሮች ከሚገኙ ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነት መመስረት አለበት፡፡ |